Ethiopian Criminal Law Network
*Hosting the past and the evolving on Ethiopian criminal law*

**ሰኔ 22/1996 ዓ.ም**

# የኢፌዲሪ የወንጀል ህግ አስመልክቶ በህግና አስተዳደር፣ በሴቶች እና በማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች ተዘጋጅቶ የቀረበ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ

## መግቢያ

በሀገራችን ዲሞክራሲያዊ ስርዓትን ለመገንባትና ፈጣን ልማትን ለማምጣት እየተደረገ ያለውን ከፍተኛ እንቅስቃሴ ከግብ ለማድረስ፣ የዓለም አቀፉንና አገራዊ ተጨባጭ ሁኔታውን መነሻ ያደረገ የብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ሉአላዊነት መገለጫ ከሆነው ህገመንግስት ጋር የተጣጠመ አዲስ ህግ ማውጣትና ነባሮችን ማሻሻል መሠረታዊ ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ፣ መንግስት የተለያዩ የህግ ጥናቶችን በማከናወን ለህዝብ ተወካዮች ም/ቤት በማቅረብ እንዲፀድቁ አድርጓል፤ በማድረግ ላይም ይገኛል::

የፍትህ ሥርዓቱን ከማሻሻል አኳያ ለረጅም ጊዜ በመንግስት ትኩረት ተሰጥቷቸው አስፈላጊ ጥናቶች ሲካሄድባቸው ከነበሩት ህጎች ውስጥ አንዱ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ነው:: የወንጀል ህግ የአንድ ሀገር ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ፣ የግለሰቦችን መብትና ነፃነቶች የሚያስከብር እንዲሁም የአገር ሰላምና ደህንነትን የሚያስጠብቅ መሆን እንደሚገባው ይታመናል:: በዚሁም መሠረት በ1949 ዓ.ም የወጣውና አሁን በሥራ ላይ ያለው የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ከወጣ በኋላ ያለውን የእድገት፣ የአስተሳሰብና ሌሎች ሁለንተናዊ ለውጦችን በተሟላ ሁኔታ ሊያስተናግድ የሚችል ሆኖ አልተገኘም::

የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት እና አገሪቱ ተቀብላ ካጸደቀቻቸው የሰብአዊ መብት ድንጋጌዎች ጋር ማጣጣም በማስፈለጉ በፍትሕ ሚኒስቴርና የህግ ስርአት ምርምር ኢንስቲትዩት የተዘጋጁ ሁለት ረቂቆች ለኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የቀረቡ ሲሆን ምክር ቤቱም መጋቢት 24/1994 ዓ.ም ባካሄደው መደበኛ ስብሰባ በረቂቆቹ ላይ ሰፊ ውይይት ካደረገ በኋላ ጉዳዩን መርምረው

ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርቡ ለህግና አስተዳደር፣ ለሴቶችና ለማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች መምራቱ ይታወሳል::

ቋሚ ኮሚቴዎቹ ከም/ቤቱ የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት ለመወጣት የህጉን ስፋትና የአገልግሎት አድማስ ከግንዛቤ ያስገባ ዕቅድ በማውጣትና በም/ቤቱ በማስፀደቅ በቀጣይነት ያደረጉት እንቅስቃሴ፣ በረቂቁ ዙርያ ተነስተው የነበሩ ዋና ዋና ጉዳዮች፣ አዲስ የተካተቱ እና ከነባር ሕጉ እንዲሠረዙ የተደረጉ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳቡ በሚከተለው ቅደም ተከተል ቀርቧል::

## 1. <u>ቋሚ ኮሚቴዎቹ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ በአግባቡ ለማዘጋጀት እንዲያስችሏቸው ያደረጓቸው እንቅስቃሴዎች</u>

ቋሚ ኮሚቴዎቹ ከአባላቱ የተውጣጣ ስራዎችን በበላይነት የሚመራ የአስተባባሪ ኮሚቴ እና አስፈላጊ የሆኑ ንኡሳን ኮሚቴዎችን በቅድሚያ ያደራጁ ሲሆን፤ ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስችል ዝርዝር ዕቅድ በማዘጋጀትና ለም/ቤቱ አቅርበው በማስጸደቅ ሥራ ጀመሩ::

በመጠቀልም ረቂቆቹ ባዘጋጁት ሁለት ተቋማት ማለትም በፍትህ ሚኒስቴር እና በፍትህና የህግ ሥርአት ምርምር ኢንስቲትዩት ባለሞያዎች አማካኝነት በተዘጋጁት ሁለት ረቂቆች መካከል ያለውን ልዩነት የም/ቤቱ አባላት ለመገንዘብ የሚያስችላቸው የ3 ቀናት ሰሚናር ተካሂዷል::

ከዚህ በተጨማሪ ከሁለቱ ተቋማት የመጡትን ረቂቆች ለማዳበር ይቻል ዘንድ አስተያየታቸውን እንዲልኩ:-

1. ለ9ኙ የፌደራሉ ክልሎች፣
2. ለአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ መስተዳድሮች፣
3. ለአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣
4. ለመቀሌ ዩኒቨርሲቲ፣
5. ለደቡብ ኒቨርሲቲ፣
6. ለኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ፣

ECLN

7. ለባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፣

8. ለዩኒቲ ኮሌጅ፣

9. ለኢትዮጵያ ህግ ባለሞያዎች ማህበር፣

10. ለኢትዮጵያ የህግ ባለሞያ ሴቶች ማህበር፣

ረቂቆቹ ተልከውላቸዋል፡፡

በዚህም መሠረት፡-

1. የደቡብ ብሔር ብሔረሰብ ህዝቦች ክልል መንግስት፣
2. የድሬዳዋ አስተዳደር ካውንስል
3. የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣
4. የኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ፣
5. የኢትዮጵያ ሴት የህግ ባለሙያዎች ማህበር፣
6. የኢትዮጵያ የህግ ባለሞያዎች ማህበር፣

ገንቢ አስተያየታቸውን ልከዋል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተለያዩ ተቋማትና ግለሰቦች በቀረቡላቸው ጥያቄዎችና በራሳቸው ተነሳሽነት በሚሻሻለው የወንጀል ህግ ዙርያ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን አስተያየት ለቋሚ ኮሚቴዎቹ ልከዋል፡፡

ከነዚህም ውስጥ፡-

1. በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል መንግሥት የፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ማስተባበሪያ ቢሮ፣
2. በጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት የሴቶች ጉዳይ ንዑስ ዘርፍ፣
3. በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የደቡብ ወሎ መስተዳድር ዞን ፍትህ መምሪያ፣
4. የኢትዮጵያ ጤና እንክብካቤ ክርስቲያን ሠራተኞች ኅብረት፣
5. የኢትዮጳያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽ/ቤት፣
6. የመጽሐፍ ቅዱስ ሠራዊት ዓለም አቀፍ ቤተክርስቲያን፣
7. የፌዴራል ሥነምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን፣
8. አክሽን የህግ የባለሙያዎች ማህበር፣
9. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ



ECLN

10. የወጣቶች ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር
11. የኢትዮጵያ መድሃኒት አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን፣
12. የህፃናት አድን ድርጅት

ይገኙበታል፡፡

የወንጀል ህጉ ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች የሚዳስስና ልዩ ትኩረት የሚሻ በመሆኑ አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ጨምሮ በሁሉም ክልሎች በአጠቃላይ 15 የውይይት ማዕከላት ተዘጋጅተው ለ3 ቀናት ውይይቶች ተካሂደዋል፡፡ በነዚህ መድረኮች ላይም ከአርሶ አደሩ፣ ከሴቶች፣ ወጣቶች ከንግዱ ህብረተሰብ፣ ከልዩ ልዩ የፍትህ አካላት ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከህክምና እና ከህግ ባለሞያዎች፣ ከወረዳ፣ ከዞን እና ከክልል የመስተዳድር አካላት፣ ከከተማ ነዋሪዎች፣ እንዲሁም ከመንግስት ሠራተኞች የተውጣጡ አብዛኛውን ህብረተሰብ ሊወክሉ የሚችሉ ተሳታፊዎች በተገኙበት ሠፊ ውይይት ተደርጓል፤ በርካታ ጠቃሚ ሀሳቦችም ተሰባስበዋል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት የውይይት መድረኮች የተዘጋጁት በአዲስ አበባ ሁለት መድረኮች፣ በአዳማ፣ በአዋሳ፣ በአርባ ምንጭ፣ በድሬዳዋ፣ በሀረር፣ በአሳይታ፣ በጋምቤላ፣ በአሶሳ፣ በባህርዳር፣ በደሴ፣ በመቀሌ፣ በጅጅጋ እና በነቀምት ሲሆኑ ለየመድረኮች ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ሀሳቦችን በመለየት፣ አስረጂ የህግ ባለሞያዎችና የኮሚቴ አባላትን በመመደብ መድረኮቹ የተሳኩ እንዲሆኑ ከፍተኛ ጥረት ተደርጓል፡፡ ከውይይቱ የተገኙ ጠቃሚ ሃሳቦችም ለረቂቁ ግብአትነት እንዲውል ተደርጓል፡፡

በነዚህ የውይይት መድረኮች ህብረተሰቡ ተወያይቶ በረቂቁ ሊካተቱ ይገባል የሚላቸውን፣ በአሠራር ያጋጠሙ ችግሮችን እና ሊሻሻሉ ይገባል የሚላቸውን በርካታ ጠቃሚ አስተያየቶች ሰጥቷል፤ በቃለ ጉባኤም እንዲያዝ ተደርጓል፡፡

ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ለማዘጋጀት የሚረዱ አስተያየቶችን ለማሰባሰብና የምክር ቤቱ አባላት ግንዛቤ ለማዳበር እንዲቻል በረቂቅ ሕጉ ዋና ዋና ጉዳዮች ማለትም፣

1. የልዩ ወንጀለኛ መቅጫ ህግ እና የደንብ መተላለፍ ህግ በረቂቅ ህጉ የሚኖራቸው ሥፍራ በአቶ ጥላሁን ተሾመ (ተባባሪ ፕሮፌሰር፣)
2. የወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሠረታውያን አምርህት በአቶ ዮሴፍ ገ/እግዚአብሄር (የህግ አማካሪና ጠበቃ) ፣
3. የኢትዮጵያ ወ.መ.ሥነ ስርአት ህግና ዋና ዋና ችግሮቹ በአቶ አበበ ሙላት፣
4. በተለያዩ ህጎች ተበታትነው የሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች እና ረቂቅ የወንጀል ህጉ በአቶ በሻደ ገመቹ፣
5. የወንጀል ቅጣት አወሳሰን ከኢትዮጵያ ወንጀል ህግ አንፃር በአቶ ጥዑመልሳን ለማ፣
6. የፅንስ ማስወረድ ወንጀል በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ በአቶ ፀሐይ ወዳ፣
7. ተሻሽለው የቀረቡት የወንጀል ህግ እና የወንጀለኛ መቅጫ ስነስርዓት ህግ ከህጉ ቴክኒክ አኳያ ሲታይ በአቶ ህጎስ ወልዱ፣
8. የወንጀል ሃለፊነትን በተመለከተ በአቶ ማርቆስ ወልደሰንበት፣
9. ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን በህግ የመከልከሉ አግባብነትና በዚሁ በኩል የወንጀለኛ መቅጫ ህጉ አስተዋፅኦ በአቶ ወንድወሰን ደምሴ፣
10. የፅንስ ማስወረድና በረቂቅ የወንጀለኛ መቅጫ የሚኖረው ሥፍራ በአቶ ጥላሁን ተሾመ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)፣
11. ከፅንስ ማስወረድ ጋር በተያያዘ ሊነሱ የሚችሉ አንዳንድ ጉዳዮች በአቶ መሃሪ ታደለ፣
12. የተሻሻለው የወንጀል ህግና የሥነስርዓት ህግ ከህፃናት መብቶች አንፃር በወ/ሮ አምሳለ ንጋቱ (ከSave the Children)

በሚሉ ርዕሶች ላይ ጥናታዊ ፅሑፎች ተዘጋጅተው የም/ቤቱ አባላት፣ የፌዴራል ዳኞች፣ ጠበቆች፣ የህግ ባለሞያ ሴቶች ማህበር፣ ሳይኪያትሪስቶች፣ የእናቶችና ህፃናት ሀኪሞች የማህፀን ሀኪሞች፣ ሶሲዮሎጂስቶች፣ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች፣ እንዲሁም ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሌሎች መንግሥታዊና

መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በጠቅላላው ከ60 በላይ የሚሆኑ የተለያዩ ባለሙያዎች የተሳተፉበት የ5 ቀናት አውደ-ጥናት ተካሂዷል፡፡

በመቀጠልም ኮሚቴዎቹ ተግባራቸውን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችላቸው የባለሞያ ድጋፍ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኙት ከፍተኛ የሞያ ብቃትና የሥራ ልምድ ያላቸውን የህግ ባለሞያዎችን በኮንትራት በመቅጠር የሚከተሉት ተግባራት እንዲከናወኑ ተደርገዋል፡፡

እነዚህም፡

ሀ. በተለያዩ መድረኮች የተሰበሰቡ የህብረተሰቡ አስተያየቶች፣

ለ. በተለያዩ ጊዜያት በምክር ቤቱ በተዘጋጁት አውደጥናቶች የተሰባሰቡ አስተያየቶች፣

ሐ. ከተለየዩ አካላት የተላኩ አስተያየቶች መጭመቅ፣

መ. በፍትህ ሚኒስቴር እና በፍትህና የህግ ሥርአት ምርምር ኢንስቲትዩት በቀረቡት ሁለት ረቂቅ ሰነዶች መካከል ያለውን ልዩነት መለየት፣

ሠ. ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው የፖሊሲ ጉዳዮቸ ለይቶ ማቅረብ፣

ረ. ለምክር ቤቱ የሚቀርበውን አንድ ወጥ የወንጀል ህግ ረቂቅ ሠነድ ማዘጋጀት፣

ሰ. የረቂቁን የእንግሊዝኛ ትርጉም ማዘጋጀት

ናቸው፡፡

ከዚህ በመቀጠል የ3ቱ ቋሚ ኮሚቴ አባላት አግባብ ካላቸው ከፍተኛ የመንግስት አካላት ጋር በመሆን በተመረጡ የፖሊሲ ጉዳዮች ዙርያ ለ2 ቀናት ውይይት አድርገዋል፡፡ በተለይም የውሳኔ ሀሳብ እንዲያዘጋጅ ከ3ቱ ቋሚ ኮሚቴዎች ተውጣጥቶ የተዋቀረው ንኡስ ኮሚቴ ረቂቆቹን አንቀጽ በአንቀጽ ከመረመረ በኋላ በተናጠልና ሥራውን ከሚመራው አስተባባሪ ኮሚቴ ጋር በመሆን የሚመለከታቸው ባለሞያዎችና የመንግስት አካላት በመጋበዝ ከረቂቆቹ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ተደጋጋሚ ውይይት አካሂዷል፡፡ በመጨረሻም የተዘጋጀው ረቂቅ የወንጀል ሕግ ለተከበረው ምክር ቤት ከመቅረቡ በፊት የፌዴራሉ የፍትሕ ሚኒስቴር አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጓል፡፡

ኮሚቴዎቹ ሥራቸውን ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን የገንዘብ ወጭ ከም/ቤቱና ከተለያዩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በማፈላለግ በሥራ ላይ እንዲውል ተደርጓል:: በዚህ አጋጣሚ አስተያየታቸውን በም/ቤት በመገኘትም ሆነ በፅሑፍ ላቀረቡልን እና በአጠቃላይ ለሥራው መሳካት አስተዋፅኦ ላደረጉ ሁሉ ምስጋናችንን እናቀርባለን::

## 2. በረቂቅ ህጉ ሰፊ ውይይት የተደረገባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች

2.1 በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች በወንጀል ተጠያቂ ይሁኑ ወይስ አይሁኑ? ተጠያቂ ይሁኑ ከተባለ የመንግስት ተቋማት እንዴት ይሁኑ?

2.2 የወንጀል ተጠያቂነት ዕድሜ መነሻ 9 ዓመት ይሁን ወይስ ከፍ ይበል?

2.3 18 ዓመት ያልሞላው ወጣት የዕድሜ ልክ እስራት እንዲቀጣ ማድረግ ከህፃናት ኮንቬንሽን ጋር ይጣጣማል ወይስ አይጣጣምም?

2.4 አካልን መሸጥ ይፈቀድ ወይስ አይፈቀድ? በስጦታ መስጠትስ?

2.5 ህግን አለማወቅና በህግ መሳሳት ሙሉ ይቅርታ ሊያሰጥ ይገባል ወይስ አይገባም?

2.6 25 ዓመት የነበረው የእስራት የቅጣት ጣሪያ ወደ 30 ዓመት ከፍ ይበል? ወይስ እንዳለ ይሁን? አጠቃላይ የቅጣት ሁኔታ ከነባሩ የወንጀለኛ መቅጫ ሁኔታ ሲታይ ረቂቅ ህጉ በመርህ ደረጃ ምን አይነት አቅጣጫ ይከተል?

2.7 የገንዘብ መቀጮ መነሻና መድረሻ ስንት ይሁን?

2.8 የቀላል እስራት መነሻና መድረሻ ስንት ይሁን?

2.9 በገንዘብ የተቀጣ ሰው መክፈል ካልቻለ መቀጫው በእስር ይለወጥ ወይስ በማህበራዊ አገልግሎት ሥራ?

2.10 የግዞት እስር ይቀጥል ወይስ ይሰረዝ?

2.11 የሞት ቅጣት ይኑር ወይስ አይኑር? ይኑር ከተባለ አፈፃፀሙ እንዴትና በምን ይሁን? የወታደርና የሲቪል ፍ/ቤት የሞት ቅጣት ውሳኔ ማን ያፅናው?

2.12 ድርጅትን በጥፋት መከልከልና መዘጋት ያለበት ስንት ዓመት በሚያስቀጣ ጥፋት መሆን ይገባዋል?

2.13 በገደብ የመልቀቅ ሁኔታ እንዴት መሆን አለበት? ፅኑ እስራትን ያካትት ወይስ አያካትት?

2.14 ዳኞችና አቃቤ ህጎችን የሚቀጣ የተለየ አንቀጽ ይኑር ወይስ አይኑር?

2.15 ዕንስ ማስወረድ በህግ ይከልከል ወይስ አይከልከል?

2.16 ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በጠቅላላው የሚያስቀጡ ይሁኑ ወይ ጎጂነታቸው በህክምና በሳይንስ የተረጋገጡ የተወሰኑት ብቻ ይካተቱ?

2.17 የቤት ውስጥ ጥቃት በረቂቁ በምን መልክ ይስተናገድ?

2.18 ጠለፋ ጋብቻን ካስከተለ የወንጀል ተጠያቂነት ማስከተል አለበት ወይስ የለበትም?

2.19 በተጋቢዎች መካከል አስገድዶ መድፈር (Marital rape) ወንጀል ሆኖ መደንገግ አለበት ወይስ የለበትም?

2.20 ዝሙት አዳሪነት በህግ ይከልከል ወይስ አይከልከል?

2.21 በጋብቻ ላይ ጋብቻ በሚመለከት በነበረው የወንጀል ህግ የተደነገገው ይቀጥል ወይስ አይቀጥል?

2.22 በዘመዳሞች መካከል የሚደረግ የግብረሥጋ ግንኙነት (incest) የጋብቻ ዘመዳሞችን ማካተት አለበት ወይስ የለበትም?

2.23 በደንብ መተላለፍ ውሣኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ጣሪያ ብር 5000 ይሁን ወይስ ከፍ ይበል?

2.24 የሽብር ተግባር በወንጀል ህጉ እንዴት ይቀረፅ? የሽብር ተግባር ሙከራ በሞት ሊያስቀጣ ይገባል ወይስ አይገባም?

2.25 ጉማ በወንጀል ህጉ መካተት አለበት ወይስ የለበትም?

2.26 እግረኛ የትራፊክ ደንብ ሲጥስ ይቀጣ ወይስ አይቀጣ?

2.27 አንድ ወንጀለኛ የፈፀመውን ወንጀል ለፍርድ ቤት ካመነ በቅጣት? ማቅለያ ይጠቃለል ወይስ አይጠቃለል?

2.28 «ቅጣት» (retribution) እንደ ዓላማ በወንጀል ህጉ ይጠቃለል ወይስ አይጠቃለል?

2.29 በውጭ አገር ወንጀል የፈፀመ ኢትዮጵያዊ የሆነ ዜጋ አሳልፎ የመስጠት ሁኔታ በወንጀል ህጉ እንዴት ይጠቃለል?

2.30 የተበዳይ ፍቃድ በወንጀል ህጉ ያስቀጣ ወይስ አያስቀጣ?

2.31 የቅጣት አወሳሰን ስርዓቱ ምን ይሁን? ማለትም የቅጣት ማኑዋል ማዘጋጀት ያስፈልጋል ወይስ አያስፈልግም? የቅጣት አማራጭ ደረጃ በደረጃ የሚታይበት ሁኔታ ይካተት ወይስ አይካተት?

2.32 በሙስና ወንጀል የተጠረጠረ ሰው ጠቃሚ ማስረጃ ከሰጠ ከወንጀል ነፃ ይሁን ወይስ አይሁን?

የሚሉና የመሳሰሉት ይገኙበታል::

ከዚህ በላይ ለተጠቀሱት ጉዳዮች ህገመንግስቱን፣ የተለያዩ ፖሊሲዎች፣ ኢትዮጵያ የፈረመቻቸውን አለማቀፍ ስምምነቶች፣ የወቅቱን ዓለምአቀፍ ሁኔታ፣ ህጉ የነበሩትን የአፈፃፀም ችግሮች፣ ወዘተ ባገናዘበ መልኩ ረቂቁ ተዘጋጅቷል::

## 3. <u>በረቂቅ የወንጀል ህጉ የተደረጉ ዋና ዋና ለውጦች</u>

3.1 **ስያሜ**:- "<u>የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የወንጀል ህግ</u>" በሚል ተሻሽሏል::

### 3.2 ቅርጽ

ረቂቅ ህጉ በ3 ታላላቅ ክፍሎችና በ8 መጽሐፍ የተከፈለ ነው:: እነዚህም፣

ሀ. የመጀመሪያው ታላቅ ክፍል (ጠቅላላ ክፍል)

1ኛ መጽሐፍ:- ወንጀሎችና ወንጀል አድራጊው

2ኛ መጽሐፍ:- የወንጀል ቅጣትና አፈፃፀሙ

ለ. ሁለተኛው ታላቅ ክፍል (ልዩ ክፍል)

3ኛ መጽሐፍ:- በመንግስት በአገርና በዓለም አቀፍ ጥቅሞች ላይ የሚደረጉ ወንጀሎች

4ኛ መጽሐፍ:- በህዝብ ጥቅሞችና በማህበራዊ ኑሮ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

5ኛ መጽሐፍ:- በሌሎች ሰዎችና በቤተዘመድ ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

6ኛ መፅሀፍ:- በንብረት ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች

ሐ. ሦስተኛው ታላቅ ክፍል (ደንብ መተላለፍ)

7ኛ መጽሐፍ:- (ጠቅላላ ክፍል) ቅጣትን የሚመለከቱ ደንቦች

8ኛ መጽሐፍ:- (ልዩ ክፍል) በህዝባዊና በማህበራዊ ጥቅሞች ላይ የሚፈጸም የደንብ ተላላፊነት የሚሉ ናቸው:: የረቂቅ ህጉ ታላቅ ክፍል

በመጽሀፍ፣ መጽሀፉ በርዕስ፣ ርዕሱ በምዕራፍ ተከፋፍሎ የተዘጋጀ ሲሆን በአጠቃላይ 863 አንቀጾችን ይዟል፡-

መ. በነባሩ ህግ «አንቀጽ» በመባል ይታወቅ የነበረው «ርዕስ» በሚል ተሻሽሎ «ቁጥር» ይባል የነበረው «አንቀጽ» ተብሎ ተሻሽሏል፡፡

የተሻሻለው ረቂቅ ሕግ ሦስት ዋና ዋና መልኮች ገጽታዎች ያሉት ሲሆን እነዚህም፡-

ሀ. ከነባሩ ህግ የተሠረዙ ወይም ወደሌላ አንቀጽ የተጠቃለሉ፣

ለ. በረቂቁ የተካተቱ አዳዲስ አንቀፆች እና፣

ሐ. ማሻሻያ የተደረገባቸው ጉዳዮችን ያካትታል፡፡ ዝርዝር ይዘታቸው በረቂቁና በሀተታ ዘምክንያቱ ተካቷል፡፡

## 3.3 በማሻሻሉ ሂደት የተሰረዙ፣ ወደ ሌላ ዓንቀፅ የተጠቃለሉ እንዲሁም በአዲስ መልክ የተቀረፁ ዋና ዋና ድንጋጌዎች

## የመጀመሪያው ታላቅ ክፍል (ጠቅላላ ክፍል)

## አንደኛ መጽሐፍ

### ሀ. የተሰረዙና ወደ ሌላ አንቀጽ የተጠቃለሉ የነባር ህጉ ድንጋጌዎች

1. **ቁጥር 42** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም የወንጀል ህጉ **አንቀጽ 43 ንዑስ አንቀጽ 2** ሆኖ በመግባቱ፣
2. በቀድሞው ህግ **ቁጥር 72** ሁለተኛው ፓራግራፍ ተደንግጎ የነበረው ስለፍትሃብሔር ጉዳይ በመሆኑ እና ይህም በፍትሃብሔር ህጉ የተካተተ በመሆኑ ተሰርዟል፡፡
3. **የቁጥር 75 ንዑስ ቁጥር 3** አንድ ሰው እራሱን በመከላከል ሂደት ለፈጸመው ጉዳት በፍትሃብሔር ተጠያቂ ከመሆን አይድንም የሚለው ስለፍትሃብሔር ጉዳይ የሚደነግግ ስለሆነ ከወንጀል ህጉ ተሠርዟል፡፡
4. **ቁጥር 77** በህግ ወንጀልነቱ ያልተደነገገን ድርጊት መፈፀም ወይም አለመፈፀም የማያስቀጣ ስለመሆኑ ይገልፅ ስለነበር ይህ ጉዳይ **በአንቀፅ 2**

(የህጋዊነት መሰረት) የተካተተ በመሆኑ ድግግሞሽን ለማስቀረት ድንጋጌው ተሰርዟል።

5. **በቁጥር 78 ላይ ንዑስ ቁጥር 3** ህግ ባለማወቅ ወይም በህግ መሳሳት አንድ ሰው በሚያስከትለው ጉዳት በፍትሃብሔር እንደሚጠየቅ የሚደነግግ ነበር። ይሁን እንጂ ጉዳዩ የወንጀል ህግ ተግባር ባለመሆኑ ድንጋጌው ተሰርዟል።

## ለ. በረቂቁ የተካተቱ አዳዲስ እና የተሻሻሉ አንቀፆች

1. በሕጉ ዓላማ(በአንቀጽ 1) ውስጥ በነባሩ ሕግ ቁጥር 1 "የወንጀለኞች መቅጫ ማረሚያ….." የሚለው ሐረግ የወንጀል ሕግ በቀጭነቱ ራሱን ችሎ እንደአላማ የሚያስቀምጥ በመሆኑ እና ይህም መቀጣጫነትን የሚያመለክት በመሆኑ መታረም አለበት። ምክንያቱም የኢትዮጵያ የወንጀል ሕግ መቀጣጫነትን እንደ አላማ አይወስድም። በመሆኑም ቅጣቱ ወንጀል አድራጊዎችን ለማረም እስካገለገለ ድረስ እንጂ እራሱን ችሎ በአላማነት መቀመጥ ስለማይገባው "….የወንጀለኞች መቅጫ፣ ማረሚያ… " የሚለው ሐረግ ቀርቶ "….ወንጀል አድራጊዎቹ ተቀጥተው ተጨማሪ ወንጀል ከመፈጸም እንዲቆጠቡ ወይም ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ …." በሚለው ሐረግ ተተክቷል።

**አንቀጽ 21 ንኡስ አንቀጽ 2** በተመለከተ

አንድን ኢትዮጵያዊ ዜጋ በሀገር ውስጥ የዳኝነት አካል እንዲዳኝ ማድረግ እንጂ አሳልፎ መስጠት አግባብነት ያለው ባለመሆኑ " …የኢትዮጵያ ዜጋ የሆነውን ማንኛውንም ሰው ለሌላ ሀገር መንግሥት አሳልፎ መስጠት አይቻልም። …." በሚል ድንጋጌ ተተክቷል።

7. የነባሩ ህግ **ቁጥር 2 ንዑስ ቁጥር 3** «ማንም ሰው በአንድ የወንጀል ስራ ሁለት ጊዜ አይቀጣም» ይላል። ይሁን እንጂ በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት **አንቀፅ 23** መሠረት ማንኛውም ሰው በህግ መሠረት ተከስሶ ጥፋተኝነቱ በተረጋገጠበት ወይም ሌላ ህጋዊ እርምጃ በተወሰደበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም የሚል ስለሆነ

ይህንን ህገመንግስታዊ መብት በግልፅ ባካተተ መልኩ ረቂቁ ተስተካክሎ **ዓንቀፅ 2 (5)** ሆኖ ገብቷል::

8. **በአንቀፅ 5** ሥር አዲስ ንዑስ **አንቀፅ 3** የተሻረው ህግ ይሰራ በነበረበት ጊዜ የተፈፀመ ወንጀል ሲኖርና በዚህ ህግ ግን እንደወንጀል ያልተቆጠረ ሲሆን ሊያስከስስም ሆነ ሊያስቀጣ አይችልም:: ክሱም ተጀምሮ ከሆነ ይቋረጣል:: በሚል ገብቷል:: ምክንያቱም ነባር ህጉ ክስ ስላልተጀመረበት ጉዳይ የሚገልፀው ነገር ስለሌለ እና አዲሱ ህግ ወንጀል አይደለም ያለው ጉዳይ ክስ ያልቀረበበትም ቢሆን ቀሪ መሆን ስላለበት ነው::

9. **በአንቀፅ 17** «በዓለም አቀፍ ህግና ሥርዓት ላይ <u>**በውጭ አገር**</u> የሚደረጉ ወንጀሎች» በሚል ስያሜ ሥር **የንዑስ አንቀፅ 1** መግቢያ ላይ «ማንም ሰው <u>**በውጭ አገር**</u> ሆኖ:-» በሚለው ውስጥ «በውጭ አገር» የሚለው ሀረግ በሌሎች ሀገሮች ግዛቶች የሚፈፀም ወንጀልን ብቻ ያመለከተ ሆኖ ይታያል:: ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ህግ Subsidiary application (በምትክነት ተፈፃሚ መሆን ያለበት) በሌሎች አገሮች ግዛት ውስጥ ለሚፈፀሙ ወንጀሎች ብቻ ሳይሆን ድርጊቶቹ የኢትዮጵያን ጥቅም የነኩ በሆኑ ጊዜ እና ከኢትዮጵያ ውጭ በየትኛውም ቦታ በተፈፀሙ ወንጀሎች ላይ መሆን ስላለበት «<u>**ማንም ሰው ከኢትዮጵያ ውጭ ሆኖ**</u>» በሚል ተስተካክሏል::

10. **በአንቀፅ 23(3)** እና በዋናነትም **በአንቀፅ 34** ላይ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች የመንግሥት አስተዳደር አካላትን ሳይጨምር በሕግ በግልጽ በተደነገገ ጊዜ በወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ ተደንግጓል::

11. **በአንቀፅ 24** የተደረጉ ለውጦች

አንቀፅ 24 (2):-አስቀድሞ የደረሰ ምክንያት እራሱን ችሎ ውጤት የሚያመጣ ከሆነ በሌላው ድርጊትና በውጤቱ መካከል ያለውን ግንኙነት ያቋርጣል፣ የሚል እና

አንቀፅ 24 (3):- የተለያዩ ምክንያቶች እራሳቸውን ችለው ውጤት ባያመጡም ተደምረው ውጤት የሚያመጡ ከሆነ ሁሉም እንደምክንያቶች ይቆጠራሉ የሚሉ ተካተዋል::

12. በነባሩ ህግ **ቁጥር 32** ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች:- በርዕሱ ላይ «ዋና ወንጀል አድራጊው እና ግብረአበሮች» የሚለው «በዋና ወንጀል አድራጊነት

ተካፋይ መሆን» በሚል ተሻሽሏል:: ምክንያቱም ይህ አንቀፅ የሚያሳየው እንደዋና ወንጀል አድራጊ እንጂ ስለተባባሪዎች ባለመሆኑ በዚሁ መልክ የረቂቁ **አንቀፅ 32** ርዕስ ሆኖ ተሻሽሏል::

13. የነባሩን ሕግ ቁጥር 48 እና 49 አስመልክቶ በነባሩ ሕግ ቁጥር 48 የተዘረዘሩት ባዮሎጂካዊ ምክንያቶች ብዙውን ጊዜ ፍጹም ኢ-ኃላፊነት እንደሚያስከትሉ ቢታወቅም የተቀነሰ ኃላፊነትን ሊያመጡ እንደሚችሉ እንደዚሁም በቁጥር 49 የተዘረዘሩት ባዮሎጂካዊ ምክንያቶች የተቀነሰ ኃላፊትን ቢያመጡም አልፎ አልፎ እነዚሁ ሁኔታዎች ለፍጹም ኢ-ኃላፊነት መነሻ ምክንያቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ይታመናል::

    በዚህም መሠረት የቁጥር 48 ስነ ሕይወታዊ ምክንያቶች የተቀነሰ ኃላፊነትንም፣ እንደዚሁም የቁጥር 49 ስነ ሕይወታዊ ምክያቶች ፍጹም ኢ-ኃላፊነትንም እንደሚያስከትሉ በሚያሳይ ሁኔታ የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ 48 እና አንቀጽ 49 ድንጋጌዎች ሆነው ተቀርጸዋል:: ምክንያቱም የነባሩ ሕግ ድንጋጌዎች ባሉበት ሁኔታ ይቀጥሉ ከተባለ የተቀነሰ ኃላፊነት ያለውና መቀጣት ያለበት ሰው በነፃ እንዲለቀቅ እንደዚሁም ፍጹም ኢ-ኃላፊ የሆነ በነፃ ሊለቀቅ የሚገባው ሰው ደግሞ እንዲቀጣ ይደረጋል:: በሌላ አነጋገር ንጹህ ሰው ወንጀለኛ ተብሎ ይቀጣል፣ ወንጀለኛው ደግሞ ንጹህ ነው ተብሎ ይለቀቃል ማለት ነው::

14. **በአንቀፅ 50** ላይ አዲስ ንዑስ **አንቀፅ 4** የተጨመረ ሲሆን፣ ምንም ጥፋት ሳይኖረው ወይም በሌላ ሰው ተገዶ በፍፁም ኢ-ሃላፊነት ውስጥ ባለበት ጊዜ ወንጀል የፈፀመ ሰው በወንጀሉ ተጠያቂ አይሆንም በሚል ተደንግጓል:: ምክንያቱም ተገዶ ህሊናውን ከሳተ በኋላ የፈፀመው ወንጀል በመሆኑ ነው::

15. **በአንቀጽ 60** ላይ አዲስ ንዑስ አንቀፅ የገባ ሲሆን ሃሳቡም «አንድ ሰው በአንድ የወንጀል ማድረግ ሀሳብ ወይም ቸልተኝነት የፈፀመው አንድን የህግ ድንጋጌ ብቻ የሚጥስ ቢሆንም አንድ አይነት ጉዳት ያስከተለው ከአንድ በላይ በሆኑ ሰዎች መብት ወይም ጥቅም ላይ ሲሆን እንደ ተደራራቢ ወንጀል ሊቆጠር እንደሚገባ የደነገገ ነው::

16. **በአንቀፅ 64** ላይ ልዩ ልዩ ተዛማጅ ያልሆኑ ተደራራቢ ወንጀሎችም እንደ አንድ የወንጀል ሀሳብ ሳይቆጠሩ እራሳቸውን ችለው እንደወንጀል እንዲቆጠሩ ተደንግጓል::

17. **አንቀጽ 65** ይህ አንቀፅ አንድ ድርጊት የተለያዩ የህግ ድንጋጌዎችን የሚጥሱ የተለያዩ ወንጀሎች ያስከተለ እንደሆነ የህግ ድንጋጌዎችን በመጣስ የሚፈፀሙ ጣምራ ወንጀሎች ሆነው በወንጀል ህጉ ገብቷል::

18. **በአንቀፅ 66**(1)ሐ ላይ በቸልተኝነት የተፈጸመ አንድ የወንጀል ድርጊት ሌላ በቸልተኝነት የሚያስቀጣ ወንጀል ሲፈጽም በተደራራቢነት እንዲያስቀጣ የሚል ተደንግጓል::

19. በቀድሞው ህግ **ቁጥር 66** ውስጥ ስለተበዳይ ፈቃድ ሲደነግግ «አድራጊው የሠራው ተግባር በህጉ ልዩ ደንብ የተከለከለና የሚያስቀጣ ከሆነ ተጎጂውም ሆነ ስለ እርሱ መብት ያለው የተስማማበት ቢሆንም ባይሆንም ከቅጣት እንደማይድን ይደነግግ ነበር:: ይሁን እንጂ ድንጋጌው በግል አቤቱታ የሚያስቀጡትንና የግል አቤቱታ ሳይቀርብ የሚያስቀጡትን ወንጀሎች በአንድነት ያካተተ ሆኖ በመገኘቱ «የተበዳይ ፈቃድ» የረቂቁ **አንቀፅ 70** በመሆን የተፈፀመው የወንጀል ድርጊት በግል አቤቱታ የሚያስቀጣና ወደ ከባድ ጉዳት የማያደርስ ድርጊት ሆኖ በተበዳዩ ወይም ስለእርሱ መብት ባለው ሰው የተፈቀደ በሆነ ጊዜ አድራጊው በወንጀል እንደማይቀጣ በንዑስ **አንቀፅ 1** ተደንግጓል:: በተጨማሪም ማንም ሰው የንግድ ዓላማ በሌለው ሁኔታ በህይወቱ እያለ ወይም ህይወቱ ካለፈ በኋላ የአካሉን፣ የአካሉን ብልት ለሚያስፈልገው ሰው ወይም ለሳይንሳዊ ምርምር በህይወት እያለ በተስማማበት ውል አሳልፎ ቢሰጥ ተቀባዩ በወንጀል የማይጠየቅ መሆኑን የደነገገ ንዑስ **አንቀፅ 2** ሆኖ ገብቷል:: ድርጊቱ የተፈፀመው በንግድ አላማ ከሆነ ግን ሰጭም ሆነ ተቀባይ በወንጀል እንዲጠየቁ በሚል ይህ አንቀፅ በአዲስ ተደንግጓል:: **(አንቀፅ 576)**

20. **አንቀፅ 75** አስገዳጅ ሁኔታን በሚመለከት የሰውን ሕይወት ወይም ደህንነት የመጠበቅ ልዩ የሙያ ግዴታ ያለበት ሰው አስገዳጅ ሁኔታን እንደምክንያት ሊቆጥር አይችልም የሚል አዲስ ፓራግራፍ ገብቷል::

21. **በአንቀፅ 82** ጠቅላላ የቅጣት ማቅለያ ምክንያቶችን የያዘ ሲሆን የነባሩን ህግ **ቁጥር 79** አንዳንድ የቃላትና የሀረግ ማስተካከያ ከማድረጉም ሌላ «አንድ ተከሳሽ አስቀድሞ ድርጊቱን ማመኑ» እንደቅጣት ማቅለያ ሆኖ **በአንቀጽ 82 (1) (ሠ)** ተደንግጓል::

22. ቅጣት ደረጃ በደረጃ ተፈጻሚ እንዲሆንና ለዚሁም ሲባል በሚወጣ ማንዋል እንዲዘረዘር ለማድረግ በአንቀጽ 88 ንዑስ አንቀጽ 3 እና 4 በመሆን እንደሚከተለው ተደንግጓል::

"3. በዚህ ሕግ በልዩ ክፍሉ ድንጋጌዎች ላይ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ቅጣት ከቀላል ወደ ከባድ በደረጃ እየታየ አግባብነት ያለው ቅጣት ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል::

ፍርድ ቤቱ ዝቅተኛውን ቅጣት አግባብነት ሳይመለከት ከፍ ያለውን ቅጣት አይወስንም::

4. የቅጣት አወሳሰንን ትክክለኛነትና አንድ ወጥነት ለማረጋገጥ (ለመቆጣጠር ) የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የቅጣት አወሳሰን መመሪያ (ማንዋል) ያወጣል::"

## <u>ሁለተኛ መጽሐፍ</u>

## ሀ. የተሰረዙና ወደ ሌላ አንቀጽ የተጠቃለሉ የነባር ህጉ ድንጋጌዎች

23. **ቁጥር 94** ተሰርዟል፤ መቀጮ ተወስኖበት በልዩ ልዩ መንገድ እንዲከፍል የተደረገው ጥረት ፍሬ ባላስገኘ ጊዜ መቀጮው በእስራት ሳይሆን በጉልበት ስራ ወይም በማህበራዊ አገልግሎት ስራ እንዲለወጥለት ተደርጓል::

24. **ቁጥር 120** (ሀ) ተሰርዟል፤ ምክንያቱም ግርፋት ኢ-ሕገመንግስታዊ በመሆኑ ነው::

25. **ከቁጥር 128** እስከ **132** ያሉት ድንጋጌዎች ተሰርዘዋል፤ ምክንያቱም ጽኑ ግዞት ከወቅቱ አስተሳሰብ ጋር የማይጣጣም እና ኋላቀር በመሆኑ ነው::

26. **ቁጥር 172** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም የአለንጋ ወይም የአርጩሜ ቅጣት ኢ-ሕገመንግሥታዊ በመሆኑ ነው::

27. **ቁጥር 205** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም **የአንቀፅ 191** እና **192** ውጤት የተለያየ በመሆኑ ውጤታቸውም በነዚሁ አንቀፆች ላይ የተጠቀሰ በመሆኑ ነው::

28. **ቁጥር 218፣ 219፣ 221 እና 222** ተሰርዘዋል። ምክንያቱም እነዚህ ድንጋጌዎች ስነስርዓታዊ ጉዳዮች በመሆናቸው እና ተገቢ ቦታቸው በሥነሥርዓት ህጉ በመሆኑ ነው።

29. **ቁጥር 232** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም የፍትሐብሔር ጉዳዮች የሚመለከት በመሆኑ ነው"

## ለ. በረቂቁ የተካተቱ አዳዲስ እና የተሻሻሉ ድንጋጌዎች

30. **በአንቀፅ 89** ላይ የቀድሞው ህግ **ቁጥር 87** የስያሜ እና አንዳንድ የቃላት ማስተካከያ ከማድረጉም ሌላ በጣም ቀላል ወንጀሎች ማለትም እስከ 3 ወር ድረስ የሚያስቀጡ ወንጀሎች መሆናቸውንና እነዚህም በተግሳፅ ወይም በማስጠንቀቂያ ሊታለፉ እንደሚቻል የደነገገ አንቀፅ ነው።

31. **በአንቀፅ 90** ላይ የገንዘብ መቀጫ መነሻ 1ብር የነበረው 10 ብር ሆኗል፤ ጣሪያው ደግሞ 5000 ሺ የነበረው 10,000 እንዲሆን ተደርጓል፤ ተቀጭው ድርጅት በህግ የሠውነት መብት የተሰጠው በሆነ ጊዜ ከ100 ብር እስከ 500,000 ብር እንዲሆን ተደርጓል።

32. **አንቀፅ 93** መቀጮ ማስገባትን የተመለከተ ድንጋጌ ሲሆን መቀጮ ወዲያውኑ መከፈል እንዳለበት እና የመክፈያ ጣራውም ከ3 ወር ወደ ስድስት ወር ከፍ እንዲል የሚደነግጉ ሁለት ንዑሳን አንቀፆች ገብተዋል።

33. **አንቀፅ 94 እና 96** በተመለከተ፡- መቀጮ ወዲያውኑ በማይከፈልበት ጊዜ ፍርድ ቤት የሚወስደውን እርምጃ የያዘ ድንጋጌ ሲሆን በተደነገገው መሠረት መቀጫን ባልፈፀመ ሠው ላይ ባልከፈለው መቀጮ መጠን ንብረቱ ተይዞ እንዲሰጥ ፍርድ ቤቱ እንዲወስን የሚያስችል አዲስ ንዑስ አንቀፅ ተካቷል።

በተጨማሪም በቁጥር 96 ላይ የግዴታ ሥራ የሚሰራ ሰው ጥፋቱ ቀላል ሲሆን ነው። በዚህ አንቀጽ መሠረት ግን ጥፋቱ ቀላልም ይሁን ከበድ ያለ የመቀጮውም መጠን አነስተኛ ይሁን ከፍ ያለ መቀጫውን መክፈል ያቃተው ሰው በአንቀጽ 93 እና 94 መሠረት የግዴታ ሥራ እንዲሰራ ሊፈረድበት ይችላል። ፍርድ ቤቱም የግዜውን ልክ መግለጽ ያለበት ሲሆን፣ የሚወሰነው ጊዜ ከ2 ዓመት ሊበልጥ እንደማይችል ተደንግጓል።

34. **በአንቀፅ 97** ላይ «የቅጣት አፈፃፀምን ማቆም» በሚለው ስያሜ ስር መቀጮው ወደ ግዴታ ሥራ ተለውጦ የተፈረደበት ሠው በድህነቱ፣ በተለያዩ ምክንያቶች… ወዘተ የግዴታ ሥራውን መቀጠል ባይችል ምን ይሁን? ለሚለው የቀድሞ ህግ ክፍተት **በአንቀፅ 105** ያለው የግዴታ ሥራ ቅጣት የሚታገድበት ሁኔታ ተፈፃሚ እንዲሆን ተደንግጓል፡፡

35. **አንቀፅ 98** «ንብረት መውረስን» በሚመለከት ፍርድ ቤት ንብረት እንዲወረስ ውሳኔ ሲሰጥ ከወንጀሉ ንጹህ የሆነ የወንጀለኛውን ባለቤት በሚመለከት ከጋራ ንብረታቸው ግማሹ እንዲሁም ንጹህን የሆኑ የወንጀል አድራጊው ባለቤት ወይም ልጆች የግል ንብረት… እንደማይወረስ በግልጽ ተደንግጓል፡፡ ምክንያቱም የንጹሃን ንብረት መወረስ ስለሌለበት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቢያንስ ከ6 ወር ወይም ፍርድ ቤቱ ሲያምንበት ከዚያ በላይ ለሆነ ጊዜ ለተቀጪው ቤተሰብ መተዳደሪያ ወይም አስፈላጊ የሆኑት የዕለት ምግብና ለኑሮአቸው መደገፊያ የሆኑ ልዩ ልዩ ገቢዎችን መወረስ እንደሌለባቸው ተሻሽሎ ተደንግጓል፡፡ ምክንያቱም በቀድሞ ሕግ የነበረው የሶስት ወር ጊዜ በቂ ስላልሆነ ነው፡፡

36. **በአንቀፅ 100** ላይ «ለመንግስት ገቢ ሊሆን የሚገባው ሀብት» በሚል ሥያሜ ሥር ያለው ድንጋጌ የቃላት ማስተካከያ ከመደረጉም ሌላ በወንጀል ተገኝቶ የተያዘ ንብረት ባለቤቱ ካልተገኘ እና ለባለቤቱ እስኪመለስ ድረስ እንዳለ ለማስቀመጥ የሚበላሽ ከሆነ በህግ መሠረት ተሸጦ ገንዘቡ ሥልጣን በተሰጠው መ/ቤት እስዘ 5 ዓመት ድረስ በአደራ ሊቀመጥ እንደሚችል የሚገልፅ አዲስ ፓራግራፍ በንዑስ **አንቀፅ 2 ሥር** ተካቷል፡፡

37. **አንቀፅ 105** የቀድሞው ህግ **ቁጥር 104** «ስለድንገተኛ ህመም» ይል የነበረው ይዘቱን ስለማይገልፅ «በህመም ጊዜ የግዴታ ሥራ ቅጣት የሚታገድበት ሁኔታ» በሚል ስያሜ **አንቀፅ 105** ሆኖ ገብቷል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ጥፋተኛው በግዴታ ሥራ ላይ እያለ ቢታመም የግዴታ ሥራውን እንዲሰራ የማይደረግ ሲሆን ከህመሙ ሲድን ግን የግዴታ ሥራውን እንዲቀጥል የሚል ተደንግጓል፡፡ ይህንን ካልቻለ ግን ከጤንነቱ ጋር የሚስማማ ሥራ እንዲሰራ ማድረግ እንጂ ወደ ገንዘብ ወይም እስራት ቅጣት መለወጡ አስፈላጊ ሆኖ ባለመገኘቱ ከላይ በተገለፀው መልክ ተስተካክሎ ተቀርጿል፡፡

38. **አንቀጽ 117፡-** የሞት ፍርድ የስቪልም ሆነ የወታደር መጽናት ያለበት በርዕሰ ብሔሩ መሆን እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ ምክንያቱም የሞት ፍርድን በተለያዩ አካላት እንዲጸና ከማድረግ ይልቅ በርዕሰ ብሔሩ መጽናቱ ስለታመነበት ነው፡፡

39 **አንቀፅ 142** በነባሩ 146 ፈቃድን ማገድና መልሶ መውሰድን የሚመለከተው ውሣኔ የተፈጥሮ ሰውን ብቻ የሚመለከት ሲሆን በህግ የሰውነት መብት የተሰጠውንም ድርጅትንም እንዲጨምር ተደርጐ ተቀርጿል፡፡

40 **አንቀጽ 146** የነባሩ ህግ ቁጥር 150 በአንድ በተወሰነ ቦታ ከመኖር ወይም ውሎ ከማደር መከልከል እስከ ዕድሜ ልክ ሊቆይ እንደሚችል የደነገገ ሲሆን እንዲህ አይነቱ ክልከላ በተከለከለው ሰው ነፃነት እና ለመታረም ባለው ዕድል ላይ ከፍተኛ ችግር የሚፈጥር በመሆኑ ክልከላው እንደ ወንጀሉ ከባድነትና ሁኔታ ከ1 ዓመት-10 ዓመት ሊደርስ እንደሚችል ሆኖ ተደንግጓል፡፡

41 **አንቀጽ 151** የነባሩ ህግ ቁጥር 155 ወንጀል የፈፀመ የውጭ አገር ዜጋን ከአገር የማስወጣት ውሣኔ አፈፃፀም በሚመለከት ንዑስ ቁጥር 3 ተቀጪው የተወሰነ ህላፊነት ያለው እንደሆነ የነገሩ ሁኔታ በቂ ምክንያት ሲያገኝ አስቀድሞ በመታከም ወይም ስለፀጥታ አጠባበቅ በተለመደው ደንብ ይለወጥለታል ይላል፡፡ የእንግሊዝኛው ቅጂ ግን «በህክምናውና በተወሰነ ቦታ መቀመጡ ቀርቶ ከአገር እንዲወጣ ይደረጋል» የሚል ነው፡፡ በቂ ምክንያት ሲኖር ከአገር እንዲወጣ ማድረጉ ተገቢ ስለሆነ የእንግሊዝኛው ትርጉም እንዲካተት ተደርጓል፡፡

የዚህ አንቀጽ ፓራግራፍ 2 ላይ ፍፁም ኢ-ህላፊ የሆነ ጥፋተኛ ከአገር የማስወጣቱ ውሣኔ በጥንቃቄ አፈፃፀም ደንብ ሊተካ ይችላል የሚለው ከላይ በተገለፀው ምክንያት ከጥንቃቄው እርምጃ እንደነገሩ ሁኔታ ከሀገር በማስወጣት ውሣኔ ሊተካ ይችላል ተብሎ ተሻሽሏል፡፡

42 **አንቀጽ 168/2** የነባሩ ህግ **ቁጥር 173/2** ለአካለመጠን ያልደረሰውን ጥፋተኛ ከ3 ዓመት በማያንስ ቅጣት ሊወስንበት እንደሚችል የተደነገገው አንዳንድ ጥፋተኞች ከተገለፀው ጊዜ ቀድመው የመታረም አዝማሚያ ቢያሳዩ ፍርድ ቤቱ ጊዜውን ለማሳጠር የማያስችለው በመሆኑ የቅጣቱ መነሻ 1 ዓመት ሆኖ እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ቅጣት ተሻሽሏል።

43 **አንቀጽ 184** ግዙፍ ወንጀሎች በተደራረቡ ጊዜ ቅጣትን ማክበድ ንዑስ **1/ሀ** የሌሎች ወንጀሎችን ቅጣት አጠቃሎ የሚይዘው የሞት ፍርድ ብቻ ስላልሆነ የሞት ከሚለው ቀጥሎ ወይም የዕድሜ ልክ እስራት ወይም ወንጀሎች ተመሳሳይ ዓይነት የእስራት ቅጣት የሚያስቀጡ ሆኖ በአንደኛ ወንጀል ምክንያት በህጉ ጠቅላላ ክፍል የተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት /አንቀጽ 106 እና 108/ ሲወስን ከዚህ በታች በፊደል «ሐ» እና «ሠ» የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ ውሣኔ ስለሌሎች ተደራራቢ ወንጀሎች የሚወሰነውን ቅጣት ሁሉ አጠቃሎ/ደርቦ ይይዛል በሚል ተሻሽሎ ቀርቧል፤ ፓራግራፍ 2 በህጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ዝቅ ብሎ የእስራት ቅጣት ከተወሰነ ግን በሌሎች ተደራራቢ ምክንያቶች ቅጣቱን እስከ ከፍተኛው ቅጣት ማሳደግ እንደሚችል ግልፅ ሆኖ ተደንግጓል። ንዑስ አንቀጽ 1/ለ ከአንድ በላይ የሆኑ ነፃነት የሚያሳጡ ተደራራቢ ወንጀሎች ባጋጠሙ ጊዜ ለእያንዳንዱ ለተፈፀመ ወንጀል ተገቢ የሆነው ቅጣት ወስጥ ሁሉት ይደመራል። ቢሆንም የቅጣቱ አይነት በህጉ ጠቅላላ ክፍል ከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት መብለጥ የለበትም በሚል ተሻሽሎ ተቀርጿል፤ ምክንያቱም በነባሩ 189/1/ለ የነበሩትን ውስብስብ አሠራሮች በማቃለል አንድ ወጥ ቀላል አሠራር ስለሚፈጥር ነው። በዚሁ ንዑስ አንቀጽ 1/ለ 2ኛ ፓራግራፍ ላይ «በፅኑ እስራትና በቀላል እስራት የሚያስቀጡ ወንጀሎች ሲፈፀሙ ለአንቀጹ አፈፃፀም የ2 ዓመት ቀላል እስራት እንደ አንድ ዓመት ቀላል እስራት እንዲቆጠር በአዲስ መልክ ተደንግጓል። ይህም በቅጣት አፈፃፀም የሚያጋጥሙ ችግሮች ለማቃለል ይረዳል። ንዑስ አንቀጽ 1/ሐ በእስራትና በመቀጮ የሚያስቀጡ ወንጀሎች ሲደራረቡ እስራቱም ሆነ ቅጣቱ ተጣምረው እንደሚወሰኑ ውሣኔውም በህጉ ጠቅላላ ክፍል መብለጥ እንደሌለበት ተደንግጓል። ይህ አቀራረፅ አወሳሰኑን ግልፅ የሚደርግ በመሆኑ ተሻሽሏል።

44. በአንድ ላይ ተጣምረው መታየት የነበረባቸው የወንጀል ክሶች በተለያዩ ፍርድ ቤቶች ወይም ችሎቶች በተናጠል ታይተው የተለያዩ ቅጣቶች በተወሰኑ ጊዜ የጠቅላላ ቅጣቱ አወሳሰን ከዚህ በላይ በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሰረት ይሆናል:: የሚል አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ገብቷል፤ ይህ አንቀጽ እስካሁን ያጋጥሙ የነበሩ ችግሮችን ለመፍታት የሚችል ንዑስ አንቀጽ ነው::

45 አንቀጽ 187 ርዕሱ በአንድ ድርጊት ጣምራ ወንጀሎች ሲፈጸሙ ቅጣት የሚከብድበት ሁኔታ በሚል ተሻሽሏል፤ ምክንያቱም notional concurence የሚለውን ቃል በተሻለ ስለሚገልጸው ነው::

በነባሩ ሕግ ቁጥር 192 ሁለቱም ዓይነት ተደራራቢ ጣምራ ወንጀሎች በግልጽ ተለይተው ባለመቀመጣቸው ያተረጓጎም ችግር ከመፍጠሩም በላይ ቅጣታቸው የተለያየ በመሆኑ በንዑስ 1 በአንድ ድርጊት በአንድ ጊዜ አደራርቦ በፈጸመው ወንጀል ከአንድ በላይ የሕግ ድንጋጌዎች ሲጥስ ስለሚወሰነው ቅጣት ንዑስ አንቀጽ 2 ደግሞ ልዩ ልዩ ግዙፍ ውጤት የሚያስከትሉ ጣምራ ወንጀሎች ሲፈጸሙ ስለሚወሰነው ቅጣት በግልጽ እንዲቀመጥ ተደርጓል:: እንዲሁም ጥፋቱ ወይም ተደራራቢ ወንጀሎቹ አስበ ወይም በቸልተኝነት ሲፈጸም ስለሚወሰኑ ቅጣቶች አስቀምጦ የበለጠ ግልጽ እንዲሆን ተደርጎ ተረቅቋል::

46 አንቀጽ 188 በነባሩ ሕግ ቁጥር 193 ውስጥ የነበሩ ግራ የሚያጋቡ ዝርዝር ነገሮች ተሰርዘው ደጋጋሚነትን በሚተረጉመው አንቀጽ 67 በተገለጹት ሁኔታዎች አንድ አዲስ ወንጀል በተፈጸመ ጊዜ ተብሎ ሲሻሻል

- ፍርድ ቤት ቅጣቱን ማክበድ ያለበት ሲሆን ለአዲሱ ወንጀል በሕጉ ልዩ ክፍል ከተደነገገው ጣራ ቅጣት በማለፍ መወሰን ይችላል የሚለው ገደብ ተሻሽሎ ለአዲስ ወንጀል የተደነገገው ጣራ ቅጣት እጥፍ እስኪሆን ሊከብድ ይችላል ተብሎ ከጠቅላላ ክፍሉ ገደብ በተጨማሪ ገደብ እንዲኖረው ተደርጓል::

- ንዑስ አንቀጽ 2 ደግሞ በከባድ ሁኔታ በጠቅላላ ክፍሉ ለቅጣቱ ዓይነት እስከተደነገገው ከፍተኛ ቅጣት ማሳደግ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

47 አንቀጽ 189 የነባሩ ሕግ ቁጥር 84 ጋር ተዛማጅ ሲሆን ተበታትነው የነበሩና ግልጽነት የጎደላቸው ድንጋጌዎች በአንድ በማስቀመጥ የተደነገገ ሲሆን፣

ንዑስ አንቀጽ "1 ቅጣት የሚያከብዱና የሚያቃልሉ ምክንያቶች በተደራረቡ ጊዜ ቅጣቱ እንዴት እንደሚላላ፣

ንዑስ አንቀጽ 2 የወንጀሎች መደራረብና ደጋጋሚነት በአንድነት ሲያጋጥሙ ቅጣቱ በምን ቅደም ተከተል እንደሚሰላ ይደነግጋል፡፡

ንዑስ አንቀጽ 3 ከወንጀሎች መደራረብና ከደጋጋሚነት ጋር የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ ምክንያቶች ሲገኙ ቅጣቱ እንዴት እንደሚሰላ በግልጽ ያስቀመጠ አንቀጽ ሲሆን ተበታትነው የነበሩትን ድንጋጌዎች በማዋሃድና አዲስ ሃሳብ በመጨመር የተቀረጸ አንቀጽ ነው፡፡

**በአንቀፅ 194 (1)** ለ. የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ቀደም ሲል አጥፊ ሆኖ ያልተቀጣ አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከ5 ዓመት ያልበለጠ ፅኑ እሥራት የሚፈረድበት ከሆነ በገደብ ሊለቀቅ እንደሚችል በአዲስ መልክ ተደንግጓል፡፡

48 አንቀጽ 201 የነባሩ ሕግ ቁጥር 206 የመጀመሪያው ፓራግራፍ በዚህ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ የተደነገገው ቅጣት ወይም "ነጻነትን የሚያሳጣ ውሳኔ'' የሚለው ሐረግ የገባው በስህተት ስለሆነ "ነጻነትን የሚያሳጣ ቅጣት ወይም የጥንቃቄ እርምጃ ... በሚል ተስተካክሏል፡፡

49. አንቀጽ 202/2 በአመክሮ ለመልቀቅ የሚያበቁ ሁኔታዎች ቢሟሉም ልማደኛ ደጋጋሚ ወንጀለኛ በአመክሮ ምንጊዜም አይፈታም የሚል አዲስ ንዑስ አንቀጽ (2) ገብቷል፡፡ ምክንያቱም ለእነዚህ ወንጀሎች የመፈታት ዕድል መስጠቱ ድርጊቱን እንዲገፉበት የሚያበረታታ በመሆኑና ከጥቅሙ ጉዳቱ ስለሚያመዝን ነው፡፡

50. አንቀጽ 204 የነባሩ ሕግ 209 2ኛው ፓራግራፍ "በጽኑ ግዞት ስፍራ ተወስኖ ከሁለት አመት ሊያንስ አይችልም" የሚለው ተሰርዟል:: ምክንያቱም በአንቀጽ 202/2 ደጋጋሚ ወንጀለኛ የአመክሮ ተጠቃሚ እንዳይሆን በመደንገጉ ነው::

በዚሁ ፓራግራፍ ውስጥ "የዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት የተፈረደበት ወንጀለኛ የአመክሮ ጊዜ ከአምስት ዓመት አይወርድም'' የሚለው ተሻሽሎ " ከአምስት ዓመት ሊያንስ ከሰባት ዓመት ሊበልጥ አይችልም" በሚል ተሻሽሏል፣ ምክንያቱም ጣራው መወሰኑ ያለአግባብ ረዥም የፈተና ጊዜ በመወሰን በግለሰቡ መብት ላይ ተጽዕኖ እንዳይባዛ ለማድረግ ነው::

51 አንቀጽ 214 የነባሩ ሕግ 223 ፍርዱ ከመወሰኑ በፊት ወንጀለኛው የሞተ እንደሆነ ክሱ አይከፈትም የሚለው ተሻሽሎ " ተከሳሽ በፍርድ ቤት ከመከሰሱ በፊት የሞተ እንደሆነ '' ክሱ ሊቀርብ ወይም ሊቀጥል ወይም ፍርድ ሊሰጥ አይችልም ተብሎ ተሻሽሏል:: ምክንያቱም ተከሳሹ ፍርድ ቤት ሳይቀርብም ሆነ ቀርቦ ፍርድ ሳይሰጥ ቢሞት ክሱ እንደሚዘጋ በግልጽ መቀመጥ ስላለበት ነው::

52 አንቀጽ 216/1 የወንጀል ክስ ይርጋ ዘመን ካለፈ ክስ መቀጠል አይቻልም የሚለው በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 28 ዘር በማጥፋት ወንጀል Genocide በዓለም ዓቀፍ ሕግ በስብዕና ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በይርጋ እንደማይታገዱ በግልጽ በመደንገጉ "በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር: የሚል ሐረግ ከፊት ለፊቱ እንዲጨመር ተደርጓል::

53 አንቀጽ 223/1 ከላይ በተጠቀሰው ምክንያት የቅጣት ይርጋም " በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተደነገገ በስተቀር'' የሚል እንዲካተት ተደርጓል"

54 አንቀጽ 229/1 ይቅርታን በሚመለከት ካለይ በተገለጸው ምክንያት "በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተገለጸ በስተቀር " የሚል ሐረግ ገብቷል::

55 አንቀጽ 230 ምሕረትም ካላይ በተገለጸው ምክንያት "በሕግ በሌላ አኳኋን ካልተገለጸ በስተቀር" በሚል ተደንግጓል።

56 አንቀጽ 233 ለመሰየም የሚያስፈልጉ ሁኔታዎች የነባሩ ሕግ 243/ሀ ቅጣቱ ጽኑ እስራትና ስለ ወንጀል ልማደኛነት.......እስከመጨረሻው ከአገር የመውጣትን ወይም የጠቅላላ መወረስን የሆነ እንደሆነ ተቀጪው የተወሰነበትን ቅጣት ከፈጸመበት ወይም ከተፈታበት ቀን ጀምሮ በጥቂቱ የአስር ዓመት ጊዜ ያለፈ እንደሆነ በሌላ ሁኔታ ሲሆን ግን ያለፈው ጊዜ በጥቂቱ አምስት ዓመት የሆነ እንደሆነ ይላል።

ሀ- ይህ ዝርዝር በቂ ባለመሆኑ

ተቀጪው የተወሰነበትን ቅጣት ከፈጸመበት ከሚለው ቀጥሎ ቅጣቱ በይርጋ ከታገደለት ወይም በይቅርታ ከተለቀቀበት ቀን አንስቶ የቅጣት ውሳኔ ወይም አፈጻጸም የታገደለት ወይም በአመክሮ የተለቀቀ ሲሆን የፈተናውን ጊዜ በመልካም ሁኔታ የጨረሰ እንደሆነ የቅጣቱ ውሳኔ ወይም አፈጻጸም ከታገደለት ወይም በአመክሮ ከተለቀቀበት ቀን ጀምሮ "ተብሎ ተጨማሪ አስፈላጊ ሁኔታዎች ተካትተዋል " ምክንያቱም በአመክሮ ወይም በይቅርታ የቅጣት አፈጻጸም የታገዱለት ሰው የፈተናውን ጊዜ በመልካም ሁኔታ ያሳለፈ ከሕብረተሰቡ ጋር በሰላም ለመኖር ፍላጎት ያሳየ ከዚያም በኋላ ለመሰየም ጊዜ መጨመሩ ተገቢ መስሎ አልታየም።

ለ. በሌላ በኩል ተቀጪው እንደጥፋቱ ክብደት ለመሰየም የ10 ዓመትና የ5 ዓመት ጊዜ እንዲጠብቅ መደረጉ አግባብ ስለማይመስል የመሰየሚያ ጊዜ በ10 ዓመት ምትክ 5 ዓመት፣ በ5 ዓመት ምትክ 2ዓመት እንዲሆን ተደርጎ ተረቋል።

ሐ- በሌላ በኩል በዚሁ ከላይ የተገለጸው አነስተኛ የመሰየሚያ ጊዜ ተፈጻሚነት የሚኖረው በዚሁ ሕግ አንቀጽ 67 ስለደጋጋሚነት የተደነገገውን የጊዜ ገደብ እስካልነካ ነው። የሚል ሃሳብ በአዲስ መልክ ገብቷል። ምክንያቱም ደጋጋሚ ነጻ ከወጣ እስከ 5 ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ መነሻ ቅጣቱ 6 ወር የሚደርስ ቀላል እስራት

የሚያስቀጣ አዲስ ወንጀል ከፈጸመ ደጋጋሚነት ወንጀል ስለሚከብድበት ነው::

57. አንቀጽ 237 የተሰጠው ውሳኔ መሻር በነባሩ ሕግ አንድ የተሰየመ ሰው በሚቀጥሉት 5ዓመታት ጊዜ ውስጥ እንደገና የሞት ቅጣት ወይም ነጻነትን የሚያሳጣ የመጨረሻ ፍርድ ተወስኖበት ከሆነ ሁለተኛ እንዲሰየም አይደረግም ይላል:: ሆኖም ነጻነትን የሚያሳጣ የሚለው ቃል ቀላል እስራትንም የሚጨምር በመሆኑ "በጽኑ እስራት" በሚል እንዲተካ ተደርጓል:: ምክንያቱም በቀላል እስራተ የተቀጣ ሰው መሰየም (ድጋሚ) መከልከሉ አግባብ መስሎ ስለማይታይ ነው:: በተጨማሪ የተፈቀደው መሰየም እንደሚሰረዝና በድጋሚም መሰየም እንደማይችል በግልጽ ተቀምጧል::

አንቀጽ 117:- የሞት ፍርድ የሲቪልም ሆነ የወታደር መጽናት ያለበት በርእሰ ብሔሩ መሆን እንዳለበት ተደንግጓል:: ምክንያቱም የሞት ፍርድን በተለያዩ አካላት እንዲጸና ከማድረግ ይልቅ በርእሰ ብሔሩ መጽናቱ ሕገ መንግሥታዊ ስለሆነና ስለታመነበት ነው::

58. በአንቀጽ 194(1) ለ. የቅጣት ገደብን አስመልክቶ ቀደን ሲል አጥፊ ሆኖ ያልተቀጣ አሁን በተከሰሰበት ወንጀል ከ5 አመት ያልበለጠ ጽኑ እስራት የሚፈረድበት ከሆነ በገደብ ሊለቀቅ እንደሚችል በአዲስ መልክ ተደንግጓል::

## ሁለተኛው ታላቅ ክፍል (ልዩ ክፍል)

## ሦስተኛው መጽሐፍ

### ሀ. የተሰረዙና ወደ ሌላ አንቀፅ የተጠቃለሉ የነባር ህጉ ድንጋጌዎች

59 **ጥር 248** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም የዚህ አንቀፅ አላማ **በአንቀፅ 84** ላይ ቅጣትን የሚያከብዱ ጠቅላላ ምክንያቶች በሚል የተመለሰ ስለሆነ ነው።

60 **ቁጥር 249** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም ዙፋን አወራረስን የሚመለከት ስለሆነ እና ኢ-ህገመንግስታዊ በመሆኑ ነው።

61 **ቁጥር 256** ተሰርዟል ምክንያቱም ርዕሰ ብሔርን ልዩ ልዩ አካላትን የሚመለከት ስድብ ወይም ስም ማጥፋት **በአንቀፅ 84 (1) ሠ** ላይ የመንግስት ባለስልጣን ወይም የስራ ግዴታውን በማከናወን ላይ በሚገኝ በአንድ የህዝብ አገልጋይ በሆነ ሠራተኛ ላይ ከሥልጣኑ ወይም ከስራው ጋር ተያይዞ ለሚሠነዘርበት ስድብ፣ ማዋረድ፣ ስም ማጥፋት በአጥፊዎች ላይ በህግ መሰረት ቅጣት እንደሚከብድባቸው ያስቀመጠ ስለሆነ ይሄው በቂ ነው ተብሎ ስለታመነበት ነው""

62 **ቁጥር 350** ተሰርዟል፣ ምክንያቱም የዚህ ድንጋጌ የቅጣት ማክበጃ ሁኔታዎች **በአንቀፅ 339** የተካተቱና ድግግሞሽ በመሆኑ ነው።

### ለ. በረቂቁ የተካተቱ አዳዲስ እና የተሻሻሉ ድንጋጌዎች

63 **አንቀጽ 241** እንዲሰረዝ፤ ምክንያቱም ሽብርተኝነትን በሚመለከት አገራችን ከፈረመቻቸው ዓለማቀፍ ስምምነቶች ጋር በተጣጣመና በተሟላ መልኩ ራሱን የቻለ ዝርዝር አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑና ዝርዝሩም በአዋጁ መካተት ስላለበት ነው።

64 **አንቀጽ 244** ይህ አንቀፅ በህገወጥ መንገድ ከአገር መውጣት፣ ወደአገር መግባት ወይም በአገሪቱ ውስጥ መኖር ወንጀል መሆኑ የሚገልፅ ነው፤ በነባሩ የወንጀለኛ መቅጫ ህግ ያልተካተተ በመሆኑ ህጉን የተሟላ ለማድረግ እነዚህ ድርጊቶች ወንጀል ሆነው በዚህ አንቀፅ ተካተዋል።

65 ወታደራዊ አገልግሎት ተግባሮችን በመጣስ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በሚል ርዕስ ሥር፡-

- **በአንቀፅ 316** በጠላት የደንብ ልብስ ወይም የጦር መሣሪያ አላግባብ መገልገል፣
- **በአንቀፅ 317** የቆሰለ ወይም የተሰዋ አባልን ትቶ መሄድ፣
- **አንቀፅ 318** የቆሰለ ወይም የተሰዋ አባል በያዘው ንብረት ላይ የሚፈጸም ወንጀል፣
- **በአንቀፅ 319** በጦር ግዳጅ ላይ የሚገኙ ሲቪሎችን ወይም ሚሊሻዎችን የሚፈጽሟቸው ወንጀሎች እንደወታደር ተቆጥረው ተጠያቂ መሆናቸውን በአዲስ መልክ ተካቷል::

**345/2** ወንጀሉ ያደረሰው ጉዳት ግንቱ እስከ 10 ሺህ ብር የሚደርስ ሲሆን በደንብ ተላላፊነት የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጓል::

66 አንቀጽ 353 (2) ማንኛውም ባለስልጣን ወይም ሠራተኛ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ግብር ወይም ቀረጥ እንዳይከፈል ወይም እንዲቀነስ ያደረገ እንደሆነ እስከ15 ዓመት ሊደርስ በሚችል ፅኑ እስራት ይቀጣል የሚል አዲስ ንኡስ አንቀፅ ተደንግጓል::

372፡- ሀሰተኛ ነገሮችን ለመስራት የሚያገለግሉ መሳሪያዎችን መስራት መያዝ በሕግ የሰውነት መብት በተሰጠው አካል ቢፈጸም የሚያስቀጣ መሆኑ ተደንግጓል::

67 አንቀፅ 354 (2) ኬላ መስበር (የኮንትሮባንድ ወንጀል የተፈፀመው) በኃይል፣ በዛቻ፣ በማጭበርበር ወይም በቡድን የተፈፀመ እንደሆነ እቃው ውርስ ሆኖ እስከ 10 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲያስቀጣ ሆኖ ተደንግጓል::

## <u>አራተኛ መጽሐፍ</u>

## <u>በረቂቁ የተካተቱ አዳዲስ እና የተሻሻሉ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀጽ 403** :- ይህ አንቀጽ ከነባር ሕጉ ቁጥር 410/1/ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ቢሆንም የስያሜና የይዘት ለውጥ ተደርጎበታል:: ስያሜው "**መሠረቱ** : ከሚል ይልቅ "**ትርጓሜ** : ቢባል የተሻለ መሆኑ ታምኖበታል:: በመንግሥት ስራ ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች በይበልጥ ግልጽ ለማድረግ በዚህ አንቀጽ ይዘት ውስጥ የመንግሥት ሠራተኛ፣ የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የመንግሥት ልማት ድርጅት፣ የሚሉትን ቃላትና ሐረጎች ከስነምግባርና ጸረሙስና አዋጆች ጋር በማዛመድ እንዲተረጎሙ ተደርገዋል::

68 **አንቀጽ 404** አንድ የተፈፀመ የሙስና ድርጊት ያለአግባብ ሰውን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት መሆኑ ከተረጋገጠ ተቃራኒ ማስረጃ እስካልቀረበ ድረስ የድርጊቱ ተፈፅሞ መገኘት ከተረጋገጠ የተፈፀመው ድርጊት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም የሦስተኛ ወገን መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት እንደሆነ ተደርጐ የህግ ግምት ሊወሰድ መቻሉን የሚደነግግ ነው::

- **አንቀጽ 405/3**:- በተከሳሹ ላይ ከሚወሰንበት ቅጣት በተጨማሪ በሕገወጥ መንገድ ያገኘው ጥቅም፣ ገንዘብ ወይም ንብረት እንዲወረስ ወይም ጥቅሙም ሆነ ንብረቱ ካልተገኘ ተመጣጣኝ ዋጋውን የሚከፍል መሆኑን እንዲያመለክት አዲስ ሆኖ ተቀርጿል::

69 **አንቀጽ 407** ይህ አንቀፅ ጉቦ መቀበልና ጉቦ መስጠት በመሳሳሉት ወይም በሙስና ወንጀሎች ተካፋይ የነበረ ሰው ክሱ ለፍርድ ቤት ከመቅረቡ በፊት ለሚመለከተው አካል በመጠቆም ድርጊቱ ተጋልጦ ለህግ እንዲቀርብ ካደረገ ከወንጀሉ ክስ ነፃ እንዲሆን የደነገገ አንቀፅ ነው::

- **አንቀጽ 409/4/**:- አንቀጽ 409/4/ በአዲስ መልክ የገባ ሲሆን ከአለም አቀፍ የንግድ ግብይት ጋር በተያያዘ የሚፈጸም የስጦታ መቀበል፣ መጠየቅ ወይም ለመጠየቅ መስማማት በተመሳሳይ እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል::

- **አንቀጽ 410/3/**:- አንቀጽ 410/3/ አዲስ ንኡስ አንቀጽ ሆኖ የገባ ሲሆን ከአለም አቀፍ የንግድ ግብይት ጋር በተያያዘ የስራ ኃላፊነት ወይም ግዴታ መነሻ የተፈጸመ በሆነ ጊዜ ቅጣት እንደሚያስከትል የሚደነግግ ሲሆን

አፈጻጸሙም በዚሁ አንቀጽ በላይኞቹ ንኡሳን አንቀጾች የተቀመጡት ቅጣቶች እንደ ሁኔታው በመውሰድ መሆኑን የሚደነግግ ነው::

- **አንቀጽ 412/3/፡-** አንቀጽ 412/3 አዲስ የገባ ንኡስ አንቀጽ ሲሆን ድርጊቱ በዚሁ አንቀጽ በንኡስ አንቀጽ 1 እንደተመለከተው ጥቅም የማግኘት ወይም የማስገኘት ሃሳብ ሳይኖር ማንኛውም ሰው እራሱ ወይም የቅርብ ዘመዱ ወይም ወዳጁ ባለጥቅም ወይም ባለአክሲዮን በሆነበት ድርጅት ወይም መስራች ወይም አባል በሆነበት የበጎ አድራጎት ድርጅትና በእርሱ መስሪያ ቤት መካከል በንግድ ወይም በሌላ ስራ፣ በግዥ ወይም በሽያጭ፣ ወይም ከሚያከናውነው ስራ ጋር የተያያዘ በማናቸውም የስራ ግንኙነት ውል እንዲፈጽም ቢያደርግ ወይም የተወሰኑ ንብረቶች እንዳይገዛ ወይም እንዳይጫረት በሕግ ወይም በደንብ ተከልክሎ እያለ በሰው ወይም በሌላ ሰው ስም ወይም ከሌላ ሰው ጋር ንብረት ቢገዛ ወይም ቢጫረት እንደሚቀጣ የሚደነግግ ነው::

70 **አንቀጽ 417** ጉዳይ ማጓተትን አስመልክቶ የተደነገገ ሲሆን፣ ማንኛውም የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራው የቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ያለውን ማንኛውንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ ወይም ከተለመደው አሠራር ውጭ ያለበቂ ምክንያት የቀረበለትን ጉዳይ ሳይወስን ቢቀር ጉዳይን በማጓተት ወንጀል በዚህ አንቀፅ በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆን ተደንግጓል::

71 **አንቀጽ 418** ይህ አንቀፅ አንድ የመንግስት ሰራተኛ ከመንግስት ከሚከፈለው ደሞዝና ሌላ ጥቅም ውጭ በሥራው አጋጣሚ ከሚያገኘው ተገልጋይ ላይ ዋጋ ያለው ነገር በነፃ ወይም አነስተኛ በሆነ ክፍያ ከፍሎ ቢያገኝ በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆን የሚያደርግ ድንጋጌ ከመያዙም ባሻገር ስጦታዎች፣ የፋይናንስ አቋምን ወይም ስጦታን መቀበልን ማስመዝገብ እንዳለበት መሆኑን የደነገገ አንቀፅ ነው::

72 **አንቀጽ 419**. አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞች ከገቢያቸው በላይ ሀብት ሲያካብቱ ይታያል:: የሀብታቸው ምንጭ እንዲህ ሊሆን የሚችለው

ስልጣናቸውን በመጠቀም ያለአግባብ ጥቅም እንደሚያገኙ ስለሚገመት ይህ ድርጊት በወንጀል እንዲቀጣ ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ በአዲስ ተደንግጐ ገብቷል፡፡ እንዲሁም ይህ አንቀጽ በመንግሥት ሠራተኛው ላይ ገቢውን እንዴት ሊያገኝ እንደቻለ የማስረዳት ሸክም ጥሎበታል፡፡

- **<u>አንቀጽ 421</u>**፡- ይህ አንቀጽ አዲስ ሲሆን፣ ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ አስቦ ብቁ ላልሆነ ወይም ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውም የንግድ ወይም የስራ ፈቃድ ቢሰጥ ወይም ቢያጸድቅ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበት ቦታ ያለአግባብ ቢፈቅድ ወይም ቢሰጥ በወንጀል ተግባር ተጠያቂ እንዲሆን ደንግጓል፡

- **<u>አንቀጽ 428/2/5/</u>**፡- አዳዲስ ንኡሳን አንቀጾች ሲሆኑ፣ ከአለም አቀፍ የንግድ ግብይት ጋር በተያያዘ ጉዳይ ለማንኛውም የሌላ አገር መንግሥት ወይም አለም አቀፍ ድርጅት ባለሥልጣን ወይም ሠራተኛ የስራ ግዴታ ማድረግ የማይገባውን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባውን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሚቀጣ፣ እንዲሁም በዚሁ አንቀጽ በንኡሳን አንቀጾቹ የተደነገጉት የጉቦ ተግባራት የህግ ሰውነት በተሰጠው ድርጅት ከሆነ በመቀጫ እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል፡፡

73 **አንቀጽ 429**. ለማንኛውም የመንግስት ስራ ለሚያከናውን ሰው ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለው ሰው ያለክፍያ ወይም በአነስተኛ ክፍያ ዋጋ ያለውን መስጠት በወንጀል የሚያስቀጣ ሆኖ አዲስ አንቀፅ ተካቷል፡፡

74 **አንቀጽ 430**. ይህ አንቀፅ «ማቀባበል» በሚል ስያሜ አዲስ የተደነገገ ሲሆን አቀባባዮች በጉቦ ሰጭና ተቀባይ መካከል ያሉ ግለሰቦች በመሆናቸው በህግ እንዲጠየቁ ማድረጉ ተገቢ ስለሆነ ወንጀል ሆኖ ተደንግጓል።

75 **አንቀጽ 431.** አንድ ቀደም ሲል የህዝብ ወይም የመንግስት አገልግሎት ሠራተኛ የነበረ ለ3ኛ ወገን በሥራው ላይ ያለ በመምሰል ሲያጭበረብር የተገኘ ወንጀል ቢፈፅም ተጠያቂ የሚሆንበት አንቀፅ እንዲካተት ተደርጓል።

- የሙስና ወንጀሎችን አስመልክቶ በመንግሥት የፖሊሲ አቅጣጫ መሰረት ተሻሽለውና ተስተካክለው እንዲቀረፁ
- የግል ድርጅቶች፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ መያዶች ወዘተ በሙስና ወንጀል ባይካተትም ጥፋት አጥፍተው ሲገኙ ቅጣቱ ከባድ እንዲሆን ቋሚ ኮሚቴዎቹ ወስነዋል።

76 **አንቀጽ 434** አንድ ሰው ህጋዊ ፈቃድ የሚጠይቅን ስራ ያለፈቃድ ወይም ከተሰጠው ፈቃድ ውጭ ቢሠራ በህግ ተጠያቂ እንዲሆን ተደርጐ የተቀረፀ አዲስ አንቀፅ ነው።

77 **አንቀጽ 439** ይህ አንቀፅ በህግ ወይም በፍርድ ቤት ሲታዘዝ አልተባበረም በማለት የመንግስት ሥራ ያሰናከለ እና ግዴታውን የጣሰ በወንጀል ተጠያቂ የሚያደርግ አዲስ ድንጋጌ ነው።

78 **አንቀጽ 445** በወንጀል ጉዳዮች ላይ ጥቆማና ማስረጃን የሚያቀርቡ እንዲሁም ምስክር ሆነው በሚቀርቡ ሀቀኛ ዜጐች ላይ የሚሠነዘሩ ጥቃቶችን ለመከላከልና ለመቅጣት የሚያስችል አዲስ አንቀፅ በወንጀል ህጉ ተካቷል።

79 **አንቀፅ 508** ለመብረር በተዘጋጀ ወይም በበራ ላይ (በአገልግሎት ላይ ያለ) የአየር መጓጓዣ ላይ በኃይል፣ በዛቻ ወይም በሌላ በማናቸውም የማስፈራሪያ ዘዴ አስቦ በህገወጥ መንገድ የያዘ ወይም በቁጥጥር ሥር ያዋለ እንደሆነ ከ15-25 ዓመት ፅኑ እስራት እንደሚቀጣ የሚደነግግ አዲስ አንቀፅ ገብቷል።

80 **አንቀፅ 509**

ሀ. በበራ ላይ ያለን አውሮፕላን አስቦ አስጊ ሁኔታ ላይ መጣል ከ15-25 ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት፣

ለ. በቸልተኝነት ከተፈፀመ ከ5-10 ዓመት የሚደርስ ፅኑ እስራት ቅጣት አዲስ ሆኖ ተደንግጓል።

81 **አንቀጽ 510**

ሀ. በአገልግሎት ላይ ያለን አውሮፕላን አስቦ ያወደመ፣ ለአገልግሎት ብቁ እንዳይሆን ያደረገ ወይም በበረራ ላይ ደህንነቱ ለአደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ የሚችል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ከ15-25 ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ የሚደነግግ አዲስ አንቀፅ ገብቷል::

ለ. ድርጊቱ የተፈፀመው በቸልተኝነት ከሆነ ደግሞ ከ5-10 ዓመት የሚደርስ ቅጣት ተደንግጓል

82 **አንቀጽ 512 (3)** አደገኛ የሆኑ ነገሮችን ወይም መሳሪያዎችን በህገወጥ መንገድ ማስቀመጥ ወይም መጫን በሚለው ርዕስ ሥር «ማንኛውም በየብስ፣ በአየር ወይም በውሃ የህዝብ ማጓጓዣዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን ለመከላከል እና ለመቆጣጠር ኃላፊነት የተጣለበት ሰው ግዴታውን በቸልተኛነት ሳይወጣ ቀርቶ በነዚሁ መጓጓዣዎች ወይም በተቋሞቻቸው ላይ አደጋ ሊያደርሱ የሚችሉ ነገሮች ወይም መሳሪያዎች ተጭነው የተገኙ እንደሆነ እስከ 5 ዓመት እንደሚቀጣ ተደንግጓል::

83 **አንቀጽ 513**

ከላይ በተጠቀሱት የአውሮፕላን ጠለፋ ድርጊቶች ውስጥ አንዱ ታስቦ ሲፈፀም በሰው ህይወት፣ ወይም ጤንነት ላይ ጉዳት የደረሰ እንደሆነ ከ10-25 ዓመት ወይም ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜ በዕድሜ ልክ ፅኑ እስራት ወይም በሞት እንዲያስቀጣ ተደንግጓል::

84 **አንቀጽ 514** በረቂቅ ወንጀል ህጉ **ከአንቀፅ 506-513** ያሉ ድንጋጌዎችን በግለሰብ ብቻ ሲፈፀሙ ሳይሆን በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸውም አካላት ህጉን ጥሰው ሲገኙ እንደማንኛውም ሰው ተጠያቂ ሊያደርግ የሚችል ድንጋጌ ተካቷል::

85 **አንቀጽ 520** የአካባቢ ብክለት በተመለከተ «ማንኛውም ሰው አግባብነት ያለውን ህግ በመተላለፍ በካይ ነገሮችን ወደ አካባቢው የለቀቀ እንደሆነ ከ10 ሺህ ብር የማይበልጥ መቀጮ ወይም ከ5 ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት እንዲቀጣ ሲደነገግ፤ ብክለቱ በሰዎች ህይወት፣ ጤና ወይም በአካባቢ ላይ ከፍ ያለ ጉዳት አድርሶ እንደሆነ ቅጣቱ ከ10 ዓመት የማይበልጥ ፅኑ እስራት እንዲያስቀጣ ሆኖ በአዲስ መልክ ተደንግጓል::

ECLN

86 **አንቀፅ 521** አደገኛ የሆነ ቆሻሻን ሌላ ቁስን በአግባቡ አለመያዝን ወንጀል የሚያደርግ አንቀጽ ገብቷል:: ቅጣቱም እስከ 5ሺህ ብር ወይም 3 ዓመት እስራት ወይም በሁለቱም ሆኖ ተደንግጓል::

87 **አንቀፅ 522** የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን የሚፃረሩ ድርጊቶች መፈፀም በወንጀል እንደሚያስቀጣ ተቀርጾ ገብቷል:: ማንም ሠው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲደረግበት በህግ የታዘዘውን ማናቸውንም ፕሮጀክት ከተገቢው አካል ፈቃድ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ወይም ሃሰተኛ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ ወንጀል ሆኖ እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል::

88 **አንቀፅ 526** ይህ አንቀፅ በቀድሞው ህግ የነበረ ቢሆንም መርዛማ ወይም የናርኮቲክ ሙድሃኒቶችን ወይም ዕፆችን ማምረት መለዋወጥ፣ ማብቀል ወይም መሥራት፣ እንዲዘዋወሩ ማድረግ በተጨማሪ በወንጀል እንዲያስቀጣ እና ቅጣቱም ከፍ እንዲል ሆኖ ተደንግጓል::

89 **አንቀጽ 527** ይህ አንቀፅ ከስፖርት ውድድር ጋር በተያያዘ ሃይል የሚጨምሩ ጉጂ የሆኑ መድሃኒቶችን ማምረትን፣ ወደአገር ማስገባትን፣ ማዘዋወርንና መሸጥን፣ መጠቀምን ለመከላከል ታስቦ የተቀረፀ ነው::

90 **አንቀጽ 531** በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅት መርዛማ ወይም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒቶችን ወይም ዕፆችን ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የከብት ድርቆሽን ወይም ሌላ መኖን የሚበክሉ ተግባራትሲፈፅሙ **በአንቀፅ 34** ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ በወንጀል ሊጠየቁ እንደሚችል ተደንግጓል::

## አምስተኛው መጽሐፍ

## ሀ. የተሰረዙ እና ወደ ሌላ አንቀፅ የተጠቃለሉ የነባር ህጉ ድንጌገዎች

91 የቁጥር **582** ድንጋጌ ተሰርዟል፣ ምክንያቱም ይህ ድንጋጌ የአንድን ሰው ግላዊ ወይም ቤተሰባዊ አኗኗር የሚመለከት አነጋገር በሀሰት ወይም በተንኮል መግለፅ እንደማይቻል ይገልፅ የነበረና ሀሳቡም በወንጀል ህጉ **በአንቀፅ 616** እና **617** ላይ የተካተተ በመሆኑ እና በድጋሚ ማስፈሩ አላስፈላጊ ስለሆነ ነው::

86 **አንቀፅ 521** አደገኛ የሆነ ቆሻሻን ሌላ ቁስን በአግባቡ አለመያዝን ወንጀል የሚያደርግ አንቀጽ ገብቷል:: ቅጣቱም እስከ 5ሺህ ብር ወይም 3 ዓመት እስራት ወይም በሁለቱም ሆኖ ተደንግጓል::

87 **አንቀፅ 522** የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን የሚፃረሩ ድርጊቶች መፈፀም በወንጀል እንደሚያስቀጣ ተቀርጾ ገብቷል:: ማንም ሠው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲደረግበት በህግ የታዘዘውን ማናቸውንም ፕሮጀክት ከተገቢው አካል ፈቃድ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ወይም ሃሰተኛ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ ወንጀል ሆኖ እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል::

88 **አንቀፅ 526** ይህ አንቀፅ በቀድሞው ህግ የነበረ ቢሆንም መርዛማ ወይም የናርኮቲክ ሙድሃኒቶችን ወይም ዕፆችን ማምረት መለዋወጥ፣ ማብቀል ወይም መሥራት፣ እንዲዘዋወሩ ማድረግ በተጨማሪ በወንጀል እንዲያስቀጣ እና ቅጣቱም ከፍ እንዲል ሆኖ ተደንግጓል::

89 **አንቀጽ 527** ይህ አንቀፅ ከስፖርት ውድድር ጋር በተያያዘ ሃይል የሚጨምሩ ጉጂ የሆኑ መድሃኒቶችን ማምረትን፣ ወደአገር ማስገባትን፣ ማዘዋወርንና መሸጥን፣ መጠቀምን ለመከላከል ታስቦ የተቀረፀ ነው::

90 **አንቀጽ 531** በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅት መርዛማ ወይም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒቶችን ወይም ዕፆችን ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የከብት ድርቆሽን ወይም ሌላ መኖን የሚበክሉ ተግባራትሲፈፅሙ **በአንቀፅ 34** ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ በወንጀል ሊጠየቁ እንደሚችል ተደንግጓል::

## አምስተኛው መጽሐፍ

## ሀ. የተሰረዙ እና ወደ ሌላ አንቀፅ የተጠቃለሉ የነባር ህጉ ድንጌገዎች

91 የቁጥር **582** ድንጋጌ ተሰርዟል፣ ምክንያቱም ይህ ድንጋጌ የአንድን ሰው ግላዊ ወይም ቤተሰባዊ አኗኗር የሚመለከት አነጋገር በሀሰት ወይም በተንኮል መግለፅ እንደማይቻል ይገልፅ የነበረና ሀሳቡም በወንጀል ህጉ **በአንቀፅ 616** እና **617** ላይ የተካተተ በመሆኑ እና በድጋሚ ማስፈሩ አላስፈላጊ ስለሆነ ነው::

86 **አንቀፅ 521** አደገኛ የሆነ ቆሻሻን ሌላ ቁስን በአግባቡ አለመያዝን ወንጀል የሚያደርግ አንቀጽ ገብቷል፡፡ ቅጣቱም እስከ 5ሺህ ብር ወይም 3 ዓመት እስራት ወይም በሁለቱም ሆኖ ተደንግጓል፡፡

87 **አንቀፅ 522** የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን የሚፃረሩ ድርጊቶች መፈፀም በወንጀል እንደሚያስቀጣ ተቀርጾ ገብቷል፡፡ ማንም ሠው የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲደረግበት በህግ የታዘዘውን ማናቸውንም ፕሮጀክት ከተገቢው አካል ፈቃድ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ወይም ሃሰተኛ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ ጉዳዩ ወንጀል ሆኖ እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል፡፡

88 **አንቀፅ 526** ይህ አንቀፅ በቀድሞው ህግ የነበረ ቢሆንም መርዛማ ወይም የናርኮቲክ ሙድሃኒቶችን ወይም ዕፆችን ማምረት መለዋወጥ፣ ማብቀል ወይም መሥራት፣ እንዲዘዋወሩ ማድረግ በተጨማሪ በወንጀል እንዲያስቀጣ እና ቅጣቱም ከፍ እንዲል ሆኖ ተደንግጓል፡፡

89 **አንቀጽ 527** ይህ አንቀፅ ከስፖርት ውድድር ጋር በተያያዘ ሃይል የሚጨምሩ ጉጂ የሆኑ መድሃኒቶችን ማምረትን፣ ወደአገር ማስገባትን፣ ማዘዋወርንና መሸጥን፣ መጠቀምን ለመከላከል ታስቦ የተቀረፀ ነው፡፡

90 **አንቀጽ 531** በህግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅት መርዛማ ወይም የናርኮቲክና ሳይኮትሮፒክ መድሃኒቶችን ወይም ዕፆችን ጉዳት ሊያደርሱ የሚችሉ የከብት ድርቆሽን ወይም ሌላ መኖን የሚበክሉ ተግባራትሲፈፅሙ **በአንቀፅ 34** ሁኔታዎች ተሟልተው ከተገኙ በወንጀል ሊጠየቁ እንደሚችል ተደንግጓል፡፡

## <u>አምስተኛው መጽሐፍ</u>

## ሀ. የተሰረዙ እና ወደ ሌላ አንቀፅ የተጠቃለሉ የነባር ህጉ ድንጌገዎች

91 የቁጥር **582** ድንጋጌ ተሰርዟል፣ ምክንያቱም ይህ ድንጋጌ የአንድን ሰው ግላዊ ወይም ቤተሰባዊ አኗኗር የሚመለከት አነጋገር በሀሰት ወይም በተንኮል መግለፅ እንደማይቻል ይገልፅ የነበረና ሀሳቡም በወንጀል ህጉ **በአንቀፅ 616** እና **617** ላይ የተካተተ በመሆኑ እና በድጋሚ ማስፈሩ አላስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡

92 **ቁጥር 595** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም በሴት ህፃናት ላይ የሚፈፀም የግበረስጋ ጥቃት ወንጀል **በአንቀጽ 630** በመካተቱ ነው::

93 **ቁጥር 596** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም ሴት ልጅን በማታለል ወይም የበታችነቷን በመጠቀም የሚለው አባባል ተገቢ ባለመሆኑና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችም **በ631** የተካተቱ በመሆኑ፣

94 **ቁጥር 597** (1) ተሰርዟል፤ ምክንያቱም የሩካቤ ስጋ ወንጀል የተፈፀመባቸው ህፃናት ከወንጀል ነፃ ስለመሆናቸው የወንጀል ህጉ **የአንቀጽ 660** አካል ሆኖ በመግባቱ ነው፣

95 **ቁጥር 597** (2) ተሰርዟል፤ ምክንያቱም ለአካለመጠን ያልደረሰች ልጅ ወደ ወንጀል ገፋፍታኛለች የሚል መከላከያ ተቀባይነት ሊኖረው ስለማይገባ ነው::

96 **ቁጥር 599** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም በሴት ላይ የተፈጸመ የግብረ ስጋ ግንኙነት በደል (ወንጀል) ጋብቻን ቢያስከትል ወንጀለኛነቱ ሊሰረዝለት ስለማይገባ፣ እንዲሁም፣ የግብረ ስጋ ግንኙነት በደል እራሱ በወንጀል አስጠያቂ እንዲሆን በመደንገጉ ነው::

97 **ቁጥር 603** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም ወንጀል ፈፃሚው ህፃን በከፊል ህላፊ ሆኖ በተገኘ ጊዜ ስለሚወሰዱ የጥንቃቄ እርምጃዎች **በአንቀፅ 49፣ 130 እና 131** ወይም በጠቅላላው ክፍል በመካተቱ ነው፤ እንዲሁም ጉዳዩ **በ590** (3) የጠለፋው ድርጊት ከወንጀል እንደማያድን በግልፅ ተደንግጓል::

98 **ቁጥር 620** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም ሴሰኛው ወንጀል የፈፀመው 15 ዓመት ባልሞላት ልጅ ላይ ከሆነ በተደራራቢ ወንጀል በሚያስቀጣ **አንቀፅ 659** ሥር በመካተቱ ነው::

ለ. በረቂቁ የተካተቱ አዳዲስ አንቀፆች እና የተሻሻሉ ድንጋጌዎች
99 ፅንስ ማስወረድን አስመልክቶ በሚከተለው ሁኔታ እንዲካተት ተደርጓል::

## ክፍል ሁለት

## በፅንስ ላይ የሚደረግ ወንጀል፤ ፅንስ ማስወረድ

**አንቀፅ 546** መርህ

1. በማናቸውም የእርግዝና ደረጃ የሚገኘውን ጽንስ **በአንቀጽ 552** ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውጭ አስቦ ማስወረድ ከዚህ በታች በተመለከቱት ድንጋጌዎች መሠረት ያስቀጣል

2. ፍርድ ቤት የቅጣቱን ዓይነትና መጠን የሚወስነው የማስወረድ ተግባሩ ታስቦ የተፈፀመው በእናቲቱ ወይም በሌላ ሦስተኛ ወገን መሆኑን፣ ድርጊቱ የተፈፀመው በሦስተኛ ወገን ከሆነ እናቲቱ ፈቅዳ ወይም ሳትፈቅድ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ይሆናል::

**አንቀጽ 547** አንዲት ሴት በራሷ ላይ የምትፈፅመው የማስወረድ ድርጊት

1. የራሷን ፅንስ አስባ በሯሷ የምታስወርድ ሴት በቀላል እሥራት ትቀጣላች
2. የማስወረጃ መሣሪያ በመስጠት ወይም ማናቸውንም ሌላ ድጋፍ በመስጠት አንዲት ሴት የፀነሰችውን ስታስወርድ በዋና ወንጀል አድራጊነት ወይም በአባሪነት ተካፋይ የሆነ ሌላ ሰው በቀላል እስራት ይቀጣል::

**አንቀጽ 548** በሌላ ሰው የሚፈፀም የማስወረድ ድርጊት

1. በህጉ ከተፈቀደው ውጭ አስቦ በፀነሰች ሴት ላይ የማስወረድ ድርጊት የፈፀመ ወይም የማስወረድ ድርጊት በሚፈፀምበት ጊዜ የረዳ በቀላል እሥራት ይቀጣል::

2. የማስወረድ ድርጊቱ የተፈፀመው ያረገዘችው ሴት ባልፈቀደችበት ወይም ፈቃዷን ለመስጠት በማትችልበት ጊዜ እንደሆነ፣ ወይም በዛቻ፣ በማስገደድ፡ በማታለል፣ ድርጊቱ የሚያስከትለውን ውጤት ለማወቅ በማትችልበት ጊዜ ፈቃዷን በማግኘት እንደሆነ፣

ቅጣቱ ከሦስት ዓመት እስከ አሥር ዓመት ለመድረስ የሚችል ፅኑ እሥራት ይሆናል።

3. በህግ ከተፈቀደው ውጭ በፈቃዷ ጽንስ ያስወረደች እርጉዝ ሴት በቀላል እስራት ትቀጣለች

**አንቀጽ 549** **ከባድ ሁኔታዎች**

**በህግ ከተደነገገው ውጭ ፅንስ የማስወረድ ተግባር የተፈፀመው**

ሀ. በአፍቅሮተ ንዋይ ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም የዘወትር ተግባሩ በማድረግ እንደሆነ /**አንቀጽ 92**/ **በአንቀጽ 548** ከተመለከተው ቅጣት በተጨማሪ በመቀጮ ይቀጣል

ለ. በቂ የህክምና ሙያ በሌለው ሰው ከሆነ ከ1 ዓመት በማያንስ እስራትና መቀጮ ይቀጣል

ሐ. በባለሙያ በተለይም በሀኪም፣ መድሃኒት ቀማሚ (ፋርማሲስት)፣ አዋላጅ ወይም አስታማሚ እንደሆነና ድርጊቱን የፈፀመውም በሙያ ሥራው ያለአግባብ በመገልገል እንደሆነ ከቀላል እስራትና መቀጮ በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛውን ለአንድ ለተወሰነ ጊዜ ወይም ወንጀሉን የደጋገመ እንደሆነ ከሙያ ስራው ለዝወትር ያግደዋል /**አንቀጽ 123**/

**አንቀጽ 550** **እርግዝና በሌላት ሴት ላይ የማስወረድ ድርጊት ለመፈፀም መሞከር**

እርግዝና በሌላት በአንዲት ሴት ላይ እርጉዝ ናት በማለት የማስወረድ ድርጊት ሙከራ የተደረገ እንደሆነ፣ ሊደረግ ስለማይቻል ወንጀል የተደነገገው ጠቅላላ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል /አንቀጽ 29/።

**አንቀጽ 551** <u>ቅጣትን የሚያቀሉ ሁኔታዎች</u>

ፅንሱ የተቋረጠው ከታች **በአንቀጽ 552** ከተዘረዘሩት ውጭ ጥልቅና በሚቆይ የኑሮ ችግር ምክንያት የሆነ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ **በአንቀጽ 180** መሰረት በመሰለው ቅጣትን ያቃልላል

**አንቀጽ 552** <u>ጽንስን ማቋረጥ ወንጀል የማይሆንባቸው ሁኔታዎች</u>

1. በሕክምና ሙያ በተፈቀደ የጊዜ ገደብ ውስጥ በህክምና ተቋም ፅንስ ሲቋረጥ በወንጀል የማያስቀጣው:-
   ሀ. በመደፈር ወይም በዘመድ መካከል በተደረገ የግብረሥጋ ግንኙነት፣
   ለ. የእርግዝናው መቀጠል በእናቲቱም ሆነ በፅንሱ ህይወት ወይም ጤንነት ላይ አደጋ የሚያስከትል ሲሆን ወይም የልጁ መወለድ በእናቲቱ ጤንነት ወይም ሕይወት ላይ አደጋ የሚያመጣ ሲሆን፤
   ሐ. ጽንሱ ሊድን የማይችል ከባድ አካል ጉድለት ያለው (ዲፎርምድ) ሲሆን፤ ወይም
   መ. አንዲት እርጉዝ ሴት የአካል ወይም የአዕምሮ ጉድለት ያለባት በመሆኗ ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰች በመሆኗ የሚወለደውን ህፃን ለማሳደግ የሀሊናም ሆነ የአካል ዝግጅት የሌላት ሲሆን ነው::
2. ከላይ በንኡስ **አንቀፅ 1** (ሀ) በተገለፁት ምክንያቶች ፅንስ ለማቋረጥ ሴትየዋ መደፈሯን ወይም ከቤተዘመድ መፀነሷን መግለጿ ብቻ በቂ ይሆናል::

**አንቀጽ 553** <u>ፅንስን የሚቋረጥበት ስነስርዓት</u>

ከላይ በአንቀጽ 552 እና ከዚህ በታች **በአንቀጽ 555** በተዘረዘሩት ሁኔታዎች መሠረት ጽንስ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር ዝርዝር መመሪያ ያወጣል::

ECLN

## አንቀጽ 554 — <u>የጤና ጥበቃ ሚኒስቴርን መመሪያ መጣስ የሚያስከትለው ቅጣት</u>

የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር በአንቀጽ 553 መሠረት ያወጣውን መመሪያ የሚጥስ ማንኛውም ሰው ከአንድ ሺህ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም እስከ ሦስት ወር መድረስ በሚችል ቀላል እሥራት ይቀጣል።

## አንቀጽ 555 — <u>ድንገተኛ /አስቸኳይ/ ሁኔታዎች</u>

በፍጥነት በሚደረግ የሕክምና ሥራ ካልሆነ በቀር ሊወገድ የማይቻል ከባድና ጊዜ የማይሰጥ አደጋ ያጋጠመ እንደሆነ ስለ አስገዳጅ ሁኔታ የተደነገገው **/አንቀጽ 75/** ተፈፃሚ ይሆናል።

100 **ከአንቀጽ 564-573** ሴትን መግረዝና በሳይንሳዊ ዘዴ ጉዳታቸው የታወቁ ድርጊቶች በወንጀል የሚያስቀጡ ሆነዋል። በዚህ አንቀጽ ጎጂ ድርጊቱን የፈፀመውም ሆነ ያስፈፀመው ተጠያቂ በሚሆኑበት ሁኔታ ተደንግጓል።

101 **አንቀጽ 564-565** በጐጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በእርጉዝ ሴትና ህፃናት ህይወት እና አካል ላይ ጉዳት ማድረስ በወንጀል የሚያስቀጡ ድርጊቶች ሆነው ተደንግገዋል።

102 **አንቀጽ 566** በጐጂ ልማዳዊ ድርጊት ፈፃሚዎች ላይ (**ከአንቀፅ 564-565** ላይ) ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲያስተላልፍ የወንጀል አድራጊውን ዕድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የኑሮ ልምድ... ወዘተ በማገናዘብ ልዩ አስተያየት ሊያደርግ እንደሚችል ተደንግጓል።

103 **አንቀጽ 567** የቤት ውስጥ ጥቃትን አስመልክቶ በወንጀል ህጉ ማንም ሰው በትዳር ጓደኛው ላይ ወይም ከጋብቻ ውጭ የግብረስጋ ግንኙት በሚኖር ሰው ላይ ጥቃት ቢያደርስ በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆን ተደንግጓል።

104 **አንቀጽ 568** በዚህ አንቀፅ ሴትን መግረዝ በየትኛውም የእድሜ ክልል ሲፈፀም ወንጀል ሆኖ ተደንግጓል።

105 **አንቀጽ 569** የሴትን ብልት መስፋት በሴት ልጅ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርስ ድርጊት በመሆኑ በወንጀል እንዲያስጠይቅ ሆኖ ተደንግጓል።

ECLN

106 **አንቀጽ 570** ከዚህ በላይ ከተቀረፁት የጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች (**አንቀፅ 564-569**) ውጭ የሆኑ ሌሎች በህክምና ጉጂነታቸው የተረጋገጠ እና በኢሰብአዊነታቸው የአካልና የአዕምሮ ጉዳትን በማስከተል የተረጋገጡ ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች በወንጀል የሚያስቀጡ ሆነው ተደንግገዋል::

107 **አንቀጽ 571፣ 572 እና 573** በጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች አማካይነት በሽታን ማስተላለፍ፣ በጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተካፋይ መሆን እና ጉጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን የሚከለክሉ ድንጋጌዎች ማነሳሳት በወንጀል የሚያስቀጡ ሆነው ተደንግገዋል::

108 **አንቀጽ 575፡-** ይህ አንቀፅ እግረኞችም ሆኑ አሽከርካሪዎች የትራፊክ ደንብ እየጣሱ በማድረስ ላይ ያሉትን የህይወት እና የንብረት እንዲሁም የአካል ጉዳት ለመከላከል የተደነገገ ነው:: እግረኞች ትክክለኛ መስመራቸውን ሳይዙ በመሄድ ወይም ባልተፈቀደላቸው መንገድ በመሄድ የተሽከርካሪዎችን እንቅስቃሴ ከመግታትም በላይ ተሽከርካሪዎች እርስበርስ በመጋጨት በእግረኞችም ሆነ በተሽከርካሪ ላይ ባሉ ሰዎችና ንብረት ላይ አደጋ ቢፈጠር ወይም አሽከርካሪዎች ህግን በመጣስ ለሚያደርሱት አደጋ ሁለቱም በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚያደርግ አዲስ አንቀፅ ነው::

109 **አንቀጽ 576** ይህ አንቀፅ የሰው አካል ወይም የአካሉ ብልት ወይም የአካሉ ክፍል በሽያጭ ማስተላለፍ እንደማይቻል የሚደነግግ አዲስ አንቀፅ ሆኖ ገብቷል::

110 **አንቀጽ 589** ለማንኛውም ዓላማ ሰውን መጥለፍ ሕገ ወጥ መሆኑ ተደንግጓል::

111 **አንቀፅ 590፡-** ይህ አንቀፅ ከነባሩ ህግ ቁጥር 558 ጋር ተወራራሽነት ያለው ሲሆን በዚህ ረቂቅ ህግ «ሴትን መጥለፍ» በሚል ርእስ ተደንግጓል:: የጠለፋውን ድርጊት ተከትሎ በጠላፊውና በተጠላፊዋ መካከል ጋብቻ ቢፈፀም እንኳ የወንጀል ተጠያቂነት ሊያስቀር እንደማይችል በግልፅ ተደንግጓል::

112 **አንቀጽ 594** ህፃንን ማለዋወጥና የራስ ያልሆነን ህፃን መውሰድ፣ አንድ ህፃን በሌላ ህፃን መለወጥ ወይም የራስ ያልሆነን ህፃን እንደራስ ልጅ አድርጎ መውሰድ በህፃናት ማዋለጃ ሀኪም ቤቶች ወይም በሌላ ቦታ ሊከሰት የሚችል በመሆኑና እንደወንጀል ሊቆጠር የሚገባው ስለሆነ አዲስ አንቀጽ ተቀርጿል፡፡

113 **አንቀጽ 600** ይህ አንቀፅ ሴትን ወይም ለአካለ መጠን ያልደረሰ ልጅን ለግዳጅ ሥራ የሚመለምልን፣ በእጁ የሚያስገባን፣ የሚደብቅን፣ ከቦታ ቦታ የሚያዘዋውርን፣ ከአገር የሚያስወጣን ወይም ወደ አገር የሚያስገባን እና ለዚህ ወንጀል የሚተባበርን ግለሰብ የሚቀጣ አዲስ አንቀፅ ነው፡፡

114 **አንቀጽ 601** ኢትዮጵያውያንን በህገወጥ መንገድ ለስራ በሚል ወደውጭ መላክ እና በዚህ ምክንያት በዜጎች ላይ እየደረሱ ያሉት የተለያዩ አደጋዎች ከጊዜ ወደጊዜ እየተስፋፉ በመምጣታቸው እነዚህ የወንጀል ድርጊቶች እንዲገቱ በወንጀል ህጉ ማካተቱ አስፈላጊ በመሆኑ ድርጊቱ በወንጀልነት፣ አድራጊውም ከአምስት እስከ 10 ዓመት ፅኑ እስራት እና እስከ ሃምሳ ሺህ ብር በሚደርስ መቀጮ እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል፡፡

115 **አንቀጽ 623 (3)** በዚህ አንቀጽ ላይ አስገድዶ መድፈሩ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ሞትን ያስከተለ ሲሆን ወይም ከወንጀሉ ጋር ተያይዞ ተበዳዩን ከህግ ውጭ ይዞ የማስቀመጥ ወይም የመጥለፍ ሌላ ወንጀል የተደረገ ሲሆን አግባብ ያላቸው ህጎች በተደራቢነት ተፈፃሚ እንደሚሆኑ እና የአስገድዶ መድፈር ወንጀል ከ5 ዓመት እስከ 15 ዓመት እንዲሆን የተደነገገ ሲሆን ነገሩ ከባድ በሆነ ጊዜም ማለትም፡-

ሀ. የተደፈረችው በሰውየው ኃላፊነት ሥር ያለች ሲሆን እና

ለ. የአካል ወይም የአዕምሮ ድክመት ያለባትን ሲሆን ወይም

ሐ. ከአንድ በላይ በሆኑ ወንዶች ህብረት በጭካኔ ወይም በማሰቃየት ሲሆን ከ5 ዓመት እስከ 20 ዓመት የሚደርስ ቅጣት እንደሚያስከትል በአዲስ ተደንግጓል፡፡

ECLN

ሐ. **አንቀጽ 624 (ሀ)** አንዲት ሴት አንድን ወንድ አስገድዳ የደፈረች እንደሆነ እስከ 5 ዓመት በሚደርስ እስራት እንድትቀጣ ተደንግጓል::

መ. **አንቀጽ 630 (ሀ)** ዕድሜዋ 13 ዓመት ያልሞላት ህፃንን የደፈረ ከ15 ዓመት እስከ 25 ዓመት ፅኑ እስራት እንዲያስቀጣ ሆኖ ተደንግጓል፣ ከባድ ጉዳት የደረሰባት ከሆነ በእድሜ ልክ ያስቀጣል::

ሠ. **አንቀፅ 634** በህፃናት ወንዶች ላይ የሚደረግ የግብረ ሰዶም ድርጊት በወንጀል ህግ እንደሚያስቀጣ ተደንግጓል::

116 ጸያፍ ወይም የብልግና ወይም ለመልካም ጸባይ ተቃራኒ የሆነ ብልግናና አሳፋሪ ስራን (pornography) በአደባባይ መፈጸም በአጠቃላይ ወንጀል ከመሆኑም ባሻገር በሕጻናት ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመካላከል **አንቀጽ 641** ንዑስ አንቀጽ 2/ሐ/ ሆኖ የሚከተለው ተደንግጓል::

"641 (2) (ሐ) ለዚሁ አላማ ሲባል አካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች የግብረስጋ ግንኙነት የፈጸሙ በማስመስል ያሳየ ወይም ሀፍረተሥጋቸው እንዲታይ ያደረገ እንደሆነ"

117 **አንቀጽ 648** ይህ አንቀፅ በተንኮል ወይም በማታለል የተፈፀመ ጋብቻ **(አንቀፅ 646)** እና በህግ የተከለከለ ጋብቻን ማስፈፀም ወይም መፈፀም የሚያስጠይቅበትን ሁኔታ የሚደነግገ ነው::

118 **አንቀጽ 659** ይህ አንቀጽ አዲስ አንቀጽ ሲሆን በተለያዩ ቦታዎች ተበታትነው የሚገኙ ድንጋጌዎች በአንድነት በማካተትና የትኞቹ ወንጀሎች እንደሚደራረቡ የሚያመላክት አጠቃላይ መርህ ለማስቀመጥ ታስቦ የተደነገገ ነው::

ECLN

## ስድስተኛ መጽሐፍ

## ሀ. የተሰረዙና ወደ ሌላ አንቀጽ የተጠቃለሉ የነባር ሕጉ ድንጋጌዎች

119 **ቁጥር 634** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም ስርቆትን የሚመለከት በአንድ አንቀፅ ሥር እንዲጠቃለል ለማድረግ ተራ ስርቆት የሚለውን **በአንቀጽ 664 ንዑስ አንቀጽ 2** ሆኖ በመግባቱ ነው::

## ለ. በረቂቁ የተካተቱ አዳዲስ እና የተሻሻሉ ድንጋጌዎች

120 **አንቀጽ 676፤** በመንግስት ወይም በህዝብ ንብረት ያላአግባብ መገልገልና ማባከን በ1949 ዓ.ም የወንጀል ህግ ላይ ያልተቀመጠ በመሆኑ ይህ ድርጊት በረቂቁ በወንጀልነት እንዲደነገግ ተደርጓል::

121 **አንቀጽ 683፣** በወንጀል የተገኘ ገንዘብን ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ መርዳት (money laundering) በዚህ ዘመን ድርጊቱ እየተስፋፋ ስለመጣ እንደወንጀል ተቆጥሮ እንዲያስቀጣ በአዲስ ተደንግጓል::

122 **አንቀጽ 693፤** በተጭበረበረ ሁኔታ የአክሲዮን ገበያን ንግድ ማካሄድ ማለትም በአክሲዮን ገበያ የሚካሄዱ ማጭበርበሮች በቀድሞው ህግ ያልተካተቱና በstock exchange ዙሪያ የሚሰሩ ወንጀሎችን መከታተልና መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በወንጀል ህጉ አዲስ አንቀፅ ሆኖ ተደንግጓል::

123 **አንቀጽ 694** በአክሲዮኖች ወይም በሸቀጦች ማምታታትን በነባሩ ህግ ያልነበረ በረቂቁ ይህ ድርጊት በወንጀልነት አስጠያቂ እንዲሆን ተደርጓል::

124 **አንቀጽ 696፤** በዚህ የወንጀል ህግ የተደነገጉት ስለአክሲዮኖች፣ ስለዕቃ ሰነዶች፣ ስለቦንዶች ወይም ስለማንኛውም የዋስትና ሰነዶች **(አንቀፅ 692-695)** የሚወጡ ሌሎች አዋጆች/ደንቦች ቢኖሩ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በቀር በዚህ ህግ ሊያስቀጡ እንደሚችሉ ሌሎች ወንጀሎች ተብሎ ተደንግጓል::

125 **አንቀጽ 705፤** ያለፈቃድ ወደ ኮምፒዩተር መግባት የኮምፒዩተር አገልግሎት ያለፈቃድ መውሰድ ወይም መጠቀም ወንጀል ሆኖ ተደንግጓል::

68. **አንቀጽ 706፤** በኮምፒዩተር፣ በዳታ ወይም በመረጃ ላይ ጉዳት ማድረስ ወንጀል ሆኖ ተቀርጿል::

69. **አንቀጽ 707፤** የተፈቀደለትን ተጠቃሚ የኮምፒዩተር አገልግሎት እንዳያገኝ ማቋረጥ ወንጀል ሆኖ ተቀርጿል::

70. **አንቀጽ 708፣** ኮምፒዩተርን መሳሪያ በማድረግ ከዚህ በላይ ከተመለከቱት ውጭ ሌሎች ወንጀሎች የተፈፀሙ እንደሆነ እነዚህ ወንጀሎች አግባብነት ያላቸው የወንጀል ህጉ አንቀጾች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ተደንግጓል::

71. **አንቀጽ 709** በኮምፒዩተር አማካኝነት የተፈፀሙ ወንጀሎች ሌሎች ወንጀሎች አስከትለው ከሆነ ሌሎች ድንጋጌዎች በተደራቢነት ተፈፃሚ እንደሚሆኑ ተደንግጓል::

723፡- በማጭበርበር ዕዳን አለመክፈል በንኡስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ተግባር በአበዳሪ ባንኮች ወይም የገንዘብ ተቋሞች ላይ ሊፈጸም ቅጣቱ እስከ 10 አመት ጽኑ እስራትና እስከ 100 ሺህ ብር ሊደርስ የሚችል ቅጣት ተደንግጓል::

## ሦስተኛው ታላቅ ክፍል ሰባተኛ መጽሀፍ

### ሀ. የተሰረዙና ወደሌላ አንቀጽ የተጠቃለሉ የነባር ህጉ ድንጋጌዎች

72. **ቁጥር 729** ተሰርዟል፤ ምክንያቱም ይህ አንቀፅ የሚገልፀው በደንብ ተላላፊነት የተከሰሰ ወይም የተቀጣ ሰው ቢሞት ስለሚያስከትለው ውጤት በመሆኑና ይህ ደግሞ **በአንቀፅ 214** እና **215** የተደነገገው በቂ በመሆኑ ድግግሞሹ መወገድ ስላለበት ነው::

73. **አንቀጽ 783፤** በወንጀል ህጉ **አንቀጽ 348** የተደነገገው ወንጀል ማለትም «በወርቅ፣ በጥሬ ገንዘብ እና በውጭ አገር ገንዘብ ህገወጥ ሥራ መሥራትን አስመልክቶ የወጣ ህግን መጣስ» **በአንቀፅ 348** ባልተሸፈኑ ጉዳዮች የሚያስቀጣ ወንጀል በሆነ ጊዜ ይሄው ተግባራዊ እንዲሆን በደንብ መተላለፍ ክፍል ገብቷል::

## በረቂቁ ላይ የተደረጉ ተጨማሪ ማስተካከያዎች

**አዲስ አንቀጽ 689 (4)** ወንጀሉ የተፈጸመው ሠውን ለመግደል፣ በአካሉ ላይ ጉዳት ለማድረስ ወይም ይዞ ለማቆየት በማስፈራራት መንግሥት፣ ሕጋዊ ሠውነት የተሰጠው አካል፣ ቡድንን ወይም ግለሰብን አንድ ነገር እንዳይፈጽም ወይም ከመፈጸም እንዲቆጠብ ለማስገደድ ታስቦ በሆነ ጊዜ ቅጣቱ እስከ 10 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 508** በኮንቲኔንታል ሽልፍ የሚገኝን ቋሚና የተተከለን ሥፍራን፣ አውሮፕላንን፣ መርከብን አላግባብ ስለመያዝ

ማንም ሰው ሕገ ወጥ በሆነ ሁኔታ ሆን ብሎ በኃይል ወይም በዛቻ ወይም በማንኛውም ማስፈራሪያ ዘዴ በኮንቲኔንታል ሽልፍ የሚገኝ ቋሚና የተተከለ ስፍራን ወይም በበረራ ላይ ያለ ወይም በማረፊያው የቆመ አውፕላንን ወይም በጉዞ ላይ ያለ ወይም በወደቡ የቆመ መርከብን በቁጥጥር ሥር ያዋለ እንደሆነ ከ15-20 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

**አንቀጽ 509** በኮንቲኔንታል ሽልፍ በሚገኝ ቋሚና የተተከለ ሥፍራን ወይም አውሮፕላንን ወይም መርከብን አስጊ ሁኔታ ላይ ስለመጣል

1. ማንም ሰው ሆን ብሎ ሕገ ወጥ በሆነ ሁኔታ በኮንቲኔንታል ሽልፍ ቋሚና የተተከለ ሥፍራ፣ በበረራ ላይ ባለ አውሮፕላን ወይም በወደብ ቆሞ ባለ መርከብ ውስጥ በሚገኝ ሰው ላይ የኃይል ሥራ ከፈጸመና ድርጊቱም የቦታውን፣ የአውሮፕላንን ወይም የመርከቡን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል የሆነ እንደሆነ ከ15-25 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡
2. ማንም ሰው በቸልተኝነት በኮንቲኔንታል ሽልፍ ቋሚና የተተከለ ሥፍራ፣ በበረራ ላይ ባለ አውሮፕላን ወይም በጉዞ ላይ ባለ መርከብ ውስጥ ባለ ሰው ላይ የኃይል ሥራ ከፈጸመና ድርጊቱ የአውሮፕላኑ ደህንነት አስጊ ሁኔታ ላይ የሚጥል የሆነ እንደሆነ ከ5-15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

**አንቀጽ 510** በኮንቲኔንታል ሽልፍ በሚገኝ ቋሚና በተተከለ ሥፍራ፣ በአውሮፕላን ወይም በመርከብ ላይ አደጋ ስለማድረስ

1. ማንም ሰው ሆነ ብሎ ሕገ ወጥ በሆነ ሁኔታ በኮንቲኔንታል ሸልፍ በሚገኝ ቋሚና የተተከለ ሥፍራ ወይም የቆመን ወይም በበረራ ላይ ያለን አውሮፕላን ወይም የቆመን ወይም በጉዞ ላይ ያለ መርከብ ላይ ጉዳት ያደረሰ ደህንነቱ ለአደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ የሚችል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ከ15-25 ሊደርስ በሚችል ጽኑ እሥራት ይቀጣል፡፡
2. ማንም ሰው በቸልተኝነት በአገልግሎት ላይ ያለን አውሮፕላን፣ መርከብ፣ ወይም በኮንቲኔንታል ስፍራ በሚገኝ የተተከለ ሥፍራን ያወደመ፣ ለበረራ ለጉዞ ወይም አገልግሎት ለመስጠት ብቁ እንዳይሆን ያደረገ ወይም የበረራ ወይም የጉዞ ደህንነቱ ለአደጋ እንዲጋለጥ ለማድረግ የሚችል ጉዳት ያደረሰ እንደሆነ ከ5-15 ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል፡፡

## በተሠራጨው ረቂቅ የተካተቱ ሌሎች አዳዲስና ለውጥ(መሻሻል) የተደረገባቸው ድንጋጌዎች

1. አንቀጽ 19 (2)
2. አንቀጽ 25 (3)
3. አንቀጽ 29 (3ኛው ፓራግራፍ)
4. አንቀጽ 35
5. አንቀጽ 43 (2)
6. አንቀጽ 44 (3)
7. አንቀጽ 46 (2ኛው ፓራግራፍ )
8. አንቀጽ 61 (2ኛው ፓራግራፍ )
9. አንቀጽ 67 (የቁጥር 82 (ለ) አሳብ የያዘ)
10. አንቀጽ 71
11. አንቀጽ 139 (2) (2ኛው ፓራግራፍ
12. አንቀጽ 194 (2) (ለ)
13. አንቀጽ 245 (1)

14. አንቀጽ 256

15. አንቀጽ 271

16. አንቀጽ 272 (1)ሐ እና (2)

17. አንቀጽ 356 (2)

18. አንቀጽ 361

19. አንቀጽ 450 (2)

20. ቁጥር 485 (5)

21. አንቀጽ 512 (1)

22. አንቀጽ 525

23. አንቀጽ 536 (3)

24. አንቀጽ 544 (3)

25. አንቀጽ 616 (4)

26. አንቀጽ 664 (2)

27. አንቀጽ 669 (መግቢያ)

28. አንቀጽ 739 (2) (2ኛው ፓራግራፍ

29. አንቀጽ 767 (1) (2ኛው ፓራግራፍ

30. አንቀጽ 769

31. አንቀጽ 828 (ሐ)

## የተሠረዙ ወይም ወደ ሌላ አንቀጾች የተጠቃለሉ ሌሎች የነባሩ ህግ ድንጋጌዎች

1. ቁጥር 57 (2) 2ኛው ፓራግራፍ

2. ቁጥር 82 (1) ወደ አንቀጽ 60 ተዛውሯል::

   ቁጥር 82 (2) ወደ አንቀጽ 189 ተዛውሯል::

3. ቁጥር 84 ወደ አንቀጽ 189 ተዛውሯል::

4. ቁጥር 89 2ኛው ፖራግራፍ ተሰርዟል

5. ቁጥር 101 (2) ተሰርዟል።

6. ቁጥር 105 (1) 2ኛው ፖራግራፍ ተሰርዟል።

7. ቁጥር 244 (2) ወደ አንቀጽ 233 ተዛውሯል።

8. ቁጥር 304 ተሰርዟል።

9. ቁጥር 318 (2) ተሰርዟል።

10. ቁጥር 587 ተሰርዟል።

11. ቁጥር 591 (2) ተሰርዟል።

12. ቁጥር 621 (2) ተሰርዟል።

13. ቁጥር 635 (3) (ሀ) ተሰርዟል።

14. ቁጥር 637 (1) (ለ) ተሰርዟል።

15. ቁጥር 648 (ለ) ተሰርዟል።

16. ቁጥር 658 (ሀ) ተሰርዟል።

## በተሠራጨው ረቂቅ ሕግ ላይ በሚገኙ ቅጣቶች ላይ የተደረጉ ማሻሻያዎች ከዚህ እንደሚከተለው ቀርበዋል።

| የነባሩ ሕግ ቁጥር | የረቂቅ ሕጉ አንቀጽ | የረቂቁ ቅጣት | የተለወጠው ቅጣት |
|---|---|---|---|
| 298 (1) | 287 (1) | እስከ 5 ዓመት ጽኑ እስራት | እስከ 3 ዓመት ቀላል እስራት |
| 298 (2) | 287 (2) | እስከ 7 ዓመት ጽኑ እስራት | እስከ 5 ዓመት ቀላል እስራት |
| 302 | 291 | ከ5 ዓመት እስከ 10 ዓመት ጽኑ | ከ3 ዓመት እስከ 10 ዓመት ጽኑ |
| 319 (1) | 307 (1) | ከ1 ዓመት እስከ 3 ዓመት ቀላል | ከ 3 ወር እስከ 3 ዓመት ቀላል አልራት |
| 322 (1) | 310 (1) | እስከ 7 ዓመት ጽኑ | እስከ 5 ዓመት ጽኑ |
| 322 (3) | 310 (3) | ታስቦ ሲሆን እስከ 15 ዓመት | ታስቦ ሲሆን እስከ 7 ዓመት ጽኑ |

ECLN

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ጽኑ<br>ከባድ ሲሆን እስከ 25 ዓመት ጽኑ | ከባድ ሲሆን እስከ 10 ዓመት ጽኑ |
| | | በቸልተኝነት ሲሆን እስከ 5 ዓመት ቀላል | በቸልተኝነት እስከ 3 ዓመት ቀላል እስራት |
| 323 (3) | 311 (3) | ለን/አ. 1 ጥፋት እስከ ስድስት ወር ቀላል<br>ለን/አ. 2 ሁለት አመት ቀላል | ለን/አ.1 እስከ አንድ አመት ቀላል |
| 330 | 322 | እስከ 50 ሺ.ህ ብር | እስከ 25 ሺ.ህ ብር |
| 348 | 340 | እስከ 200 ሺ.ህ ብር | እስከ 100 ሺ.ህ ብር |
| 357 | 348 | እስከ 10 ዓመት ጽኑ እና እስከ 50 ሺ.ህ ብር | እስከ 10 ዓመት ጽኑ እስራትና እስከ 50 ሺ.ህ ብር |
| 361 | 352(1) | ከ3 ዓመት በማያንስ ቀላል እና በመቀጮ | ከአንድ ዓመት እስከ 3 ዓመት ቀላል እና በመቀጮ |
| 369 (1) | 362 (1) ለ | በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ | እስከ 5 ዓመት ቀላል እስራት ወይም በመቀጮ |
| 381 (2) | 374 | በእፍቅሮ ንዋይ ሲሆን እስከ 200.000 ብር ሀሰተሀኛ ገንዘብ ሲሰራ እስከ 500.000 ብር | - እስከ 100.000 ብር<br>- እስከ 250.000 ብር |
| 390 (2) ፓራ(1) | 383 (2) | እስከ 15 ዓመት ፅኑ እስራት | እስከ 10 ዓመት ፅኑ እስራት |
| 393 (1) | 386(1) | - ከ1 ዓመት እስከ 3 ዓመት ቀላል እስራት | እስከ 10 ዓመት ፅኑ እስራት<br>ከስድስት ወር የማያንስ እስራት |
| 393(2) ፓራ (1) | 386 (2) | ከ6 ወር እስከ 3 ዓመት ቀላል እስራት | ከ6 ወር እስከ 5 ዓመት ቀላል እስራት |
| 495 (2) | 502(2) | እስከ 3 ዓመት ቀላል እስራት | እስከ 1 ዓመት ቀላል እስራት |
| 496 (2) | 503 (2) | እስከ 3 ዓመት ቀላል እስራት | እስከ 1 ዓመት ቀላል እስራት |
| 500 | 507 (2) | እስከ 15 ዓመት ቀላል እስራት | እስከ 10 ዓመት ቀላል እስራት |
| 506 | 518 (2) | እስከ 25 ዓመት ፅኑ እስራት | እስከ 15 ዓመት ፅኑ እስራት<br>ለከባድ ሁኔታ የሚለው ቅጣት ተሰርዟል |
| የለም | 564 | ሰው በመግደል ይጠየቃል | - ከ3 ወር -1ዓመት ቀላል<br>- ቸልተኝነት ሲኖር<br>- በቸልተኝነት ግድያ |
| የለም | 565 | ሰው በመግደል ይጠየቃል | - ን/አ 1 - እስከ 6 ወር ቀላል እስራት<br>- ን/አ2 ቸልተኝነት ሲኖር በቸልተኝነት አንቀጽ ይጠየቃል |
| 552 | 583 | እስከ 1 ዓመት ወይም እስከ ሺ. ብር | እስከ 6 ወር ቀላል ወይም<br>እስከ 500 ብር |
| 558(1) | 590 (1) | ከ7 ዓመት እስከ 10 ዓመት | ከ3 አመት እስከ 10 ዓመት ፅኑ |
| 559 | 591 | እስከ 10 ዓመት ፅኑ እስራት | ከ3 አመት እስከ 15 ዓመት ፅኑ እስራት |
| 580 (1) | 616 (1) | እስከ 1 ዓመት ቀላል ወይም በመቀጮ | ከ6 ወር በማያንስ ቀላል እስራት ወይም መቀጮ |
| 580 (2) ፓራ 1 | 616 (2) | ከ 3ወር በማያንስ ቀላል ወይም በመቀጮ | ከ1 ወር በማያንስ ቀላል እስራት ወይም መቀጮ . |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 580 (3) ፓራ 2 | 616 (3) | ከ 6ወር በማያንስ ቀላል እስራትና መቀጮ | ከ3 ወር የማያንስ ቀላል እስራትና በመቀጮ |
| 586 (ሀ) | 621 (ሀ) | እስከ 6 ወር ቀላል ወይም እስከ ሺ ብር | እስከ 5 ወር ቀላል እስራትና እስከ ሺህ ብር መቀጮ |
| (ለ) | (ለ) | ከ3ወር እስከ 1 ዓመት ቀላል እስራትና መቀጮ | እስከ 1 አመት ቀላል እስራትና መቀጮ |
| (ሐ) 1ኛ ዐ.ነ | (ሐ) | ከ6 ወር በማያንስ ቀላል እስራት | ከ3 ወር በማያንስ ቀላል እስራትና መቀጮ |
| ሐ) 2ኛ ዐ.ነ | (መ) | ከ9 ወር በማያንስ ቀላል እስራትና መቀጮ | ከ6 ወር በማያንስ ቀላለ እስራትና በመቀጮ |
| 589 (2) | 623 (2) | እስከ 20 ዓመት ፅኑ እስራት | ከ 5ዓመት እስከ 20 ዓመት ፅኑ እስራት |
| | 634 (1) | ከ 5 ዓመት እስከ 25 ዓመት | ከ15 ዓመት እስከ 25 ዓመት |
| 654 | 689 | እስከ 5 ዓመት ፅኑ እስራትና መቀጮ | 1) ሀ እና ሐ እስከ 7 ዓመት ፅኑ እስራት<br>2) ለ እስከ 10 ዓመት ፅኑ እስራት<br>ነገሩ ሲከብድ እስከ 20 ዓመት ፅኑ እስራት |
| 666 (ለ) | 704(ለ) | በመቀጮ | በቀላል እስራት ወይም በመቀጮ |

* ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ውጭ በረቂቁ ውስጥ በጥቁርና በነጭ በአማራጭ ከተቀመጡት ቅጣቶች ውስጥ የተለየ ሁኔታ ካላጋጠመ በስተቀር ቋሚ ኮሚቴዎቹ ዝቅተኛ የሆነውን ቅጣት መርጠዋል::

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች በቀድሞው ህግ ውስጥ የነበሩና አሁን ግን የተሠረዙ፣ ወደሌላ አንቀጽ የተጠቃለሉ እና አዳዲስ የገቡ አንቀፆች ቢሆኑም ከነዚህ ሌላ በዚሁ መልክ የተሰረዙ የተሻሻሉ እና በአዲስ የገቡ በርካታ ንዑሳን አንቀፆች በመኖራቸው ዝርዝራቸውን ከሀተታ ዘምክንያቱ መመልከት ይቻላል::

ከዚህም ባሻገር የ1949 ዓ.ም የወንጀለኛ መቅጫ ሕግና የተሻሻለውን ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የተሻሩ ሲሆን በዚህ የወንጀል ሕግ በግልጽ ያልተሸፈኑ ዝርዝር ጉዳዮችን የያዙ ሕጎች የተጠበቁ ናቸው::

## የውሳኔ ሀሳብ

የኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ም/ቤት ከ1949 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የሚገኘውን የወንጀለኛ መቅጫ ህግን ለማሻሻል ታስቦ በመንግስት ተዘጋጅተው የቀረቡትን ሁለት ረቂቅ የወንጀል ህጎችን የህግና አስተዳደር፣ የሴቶች እና የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች መርምረው ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ እንዲያቀርቡለት በሰጠው መመሪያ መሠረት የተለያዩ ተግባራትን ሲያከናውኑ ቆይተዋል::

ከነዚህም ተግባራት ውስጥ:-

1ኛ. የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች እና ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸው አካላት እና ባለሞያዎች ተሳትፎን በማረጋገጥ ረቂቅ ህጉን ለማዳበር የሚያስችል ግብአት ማሰባሰብ፣

2ኛ. የፖሊሲ ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮችን የመለየትና ውሳኔ የመስጠት፣

3ኛ. በፍትህ ሚኒስቴር እና በፍትህና የህግ ሥርዓት ምርምር ኢንስትቲዩት የተዘጋጁትን ሁለት ረቂቆች ወደ አንድ የተጠናከረ ረቂቅ የማጠቃለል ሥራ፣

4ኛ. አስፈላጊውን ጊዜ በመመደብ ረቂቅ ህጎቹን አንቀፅ በአንቀፅ መመርመር፣

5ኛ. በነባሩ ህግ የሚገኙትን የተለያዩ አንቀፆች የበለጠ ግልፅ ማድረግ፣

6ኛ. ከህገመንግስቱ ጋር የማይጣጣሙ የነባሩን ህግ አንዳንድ አንቀፆች የመሠረዝ እና ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር ማጣጣም፣

7ኛ. አገራዊና አለም አቀፋዊ ሁኔታን መነሻ በማድረግ አስፈላጊ የሆኑ አዳዲስ ጉዳዮችን በረቂቁ እንዲካተቱ ማድረግ እና አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮች በረቂቁ እንዲካተቱ ማድረግ እንዲሁም ቅጣት መስተካከል በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ የማስተካከል ስራ መስራት::

8ኛ. በተለያዩ አዋጆች ተበታትነው የሚገኙ የወንጀል ህግ ድንጋጌዎች በተቻለ መጠን በማሰባሰብ እና ህጉን ኮምፕሬሄንሲቭ የማድረግ ሥራዎች ተሰርተዋል::

ቋሚ ኮሚቴዎቹ ብቃት ባላቸው ባለሞያዎች ታግዘው ያዘጋጁትን ረቂቅ የወንጀል ህግ እነሆ ለም/ቤቱ ውሳኔ የቀረበ ሲሆን ሀተታ ዘምክንያቱም ከዚህ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ ጋር ተያይዞ ቀርቧል::

የወንጀል ሕጉ ከግንቦት 1/1997 ዓ.ም ጀምሮ ሥራ ላይ የሚውል መሆኑን ኮሚቴዎቹ ተስማምተዋል::

ስለሆነም የተከበረው ም/ቤት የቀረበውን ረቂቅ የወንጀል ህግእንዲሁም ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ እንዲያፀድቀው እንጠይቃለን::

የህግና አስተዳደር፣ የሴቶችና የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴዎች

ECLN